# የወላጅ መብቶች
## የሜሪላንድ የሥርዓት መከላከያ ማስታወቂያ



**የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል**
**Maryland State Department of Education**
**የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች**
**Division of Special Education/Early Intervention Services**

ጁላይ 1፣ 2007 ዓ.ም.

Maryland State Department of Education
Division of Special Education/Early Intervention Services
200 West Baltimore Street
Baltimore, MD 21201
410-767-0858 (ስልክ)
410-333-1571(ፋክስ)
http://marylandpublicschools.org

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ሥራ ቅጥርን ወይም በአንዳንድ የመርሀ-ግብር ተሳትፎዎችን በተመለከተ ተጸዕኖ ሊያሳድር የሚችል በጎሳ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በብሄር፣ በሃይማኖት ወይም በአካለ ስንኩልነት ላይ የተመሠረተ ምንም ዓይነት አድሎ አያደርግም። የክፍሉን አመራር በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት የእኩልነት ማረጋገጫና መፈጸሚያ ቅርንጫፉን (Equity Assurance and Compliance Branch) በስልክ ቁጥር (410) 767-0433 በመደወል ወይም በፋክስ ቁጥር (410) 767-0431 መገናኘት ይችላሉ። የአካል ጉድለት ያለባቸው አሜሪካዊያን (Americans with Disabilities Act (ADA)) በደነገገው መሠረት ይህ ሰነድ በተጠየቀ ጊዜ በአማራጭ አቀራረቦች ዝግጁ ሆኖ ይገኛል። የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚገኘውን የልዩ ትምህርት/ቅድመ ገላጋይ አገልግሎቶችን ክፍል በስልክ ቁጥር (410) 767-0858 ወይም በፋክስ (410) 333-1571 ይገናኙ።

ይህ ሰነድ ከዩ.ኤስ. የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርትና የመቋቋሚያ አገልግሎቶች በተገኘ ገንዘብ፣ በልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች፣ IDEA ክፍል B ችሮታ #HO27A060035A መሠረት ዳብሮና ታትሞ የተዘጋጀ ነው። የልዩ ትምህርት/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ክፍል በዩ.ኤስ. የትምህርት ክፍል ሥር ከሚገኙት የልዩ ትምህርት መርሃ-ግብሮች፣ የልዩ ትምህርትና የመቋቋሚያ አገልግሎቶች ቢሮ የገንዘብ እርዳታ ያገኛል። ይህ መረጃ ከሕትመት ሕግ (ኮፒራይት) ነጻ ነው። አንባቢዎች አባዝተው እንዲጋሩት ይበረታታሉ ሆኖም ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ገላጋይ አገልግሎቶች መምጣቱን እባክዎን ያስታውቁ።

## ማውጫ


**የሥርዓት መከላከያዎች ... 1**

**የትውልድ ቋንቋ ... 1**

**ኢ-ሜል ... 1**

**ቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ... 2**

ማስታወቂያ ... 2

የጽሑፍ ማስታወቂያ ይዞታ ... 2

**ስምምነት ... 2**

የመጀመሪያውን ግምገማ ለማድረግ የወላጅ ስምምነት ... 3

በመንግሥት አሳዳጊነት ሥር ላሉ የመጀመሪያ ግምገማ ለመስጠት ያሉ ልዩ ሕጎች ... 3

ለአገልግሎቶች የወላጅ ስምምነት ... 3

ለዳግም ግምገማዎች የወላጅ ስምምነት ... 3

የወላጅ ስምምነትን ለማግኘት የተደረጉ ተገቢ ጥረቶችን መመዝገብ ... 4

ሌሎች ለስምምነት መሟላት ያለባቸው ነጥቦች ... 4

**በግል የሚደረግ የትምህርት ግምገማ ... 4**

ፍቺዎች ... 4

የሕዝብ ድርጅት መመዘኛዎች ... 4

በሕዝብ ወጪ የሚደረግ ግምገማ ጋር የተያያዘ የወላጅ መብት ... 5

በወላጅ አነሳሽነት የሚደረግ ግምገማ ... 5

ግምገማ በአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ) እንዲደረግ ስለመጠየቅ ... 5

**መረጃን በግልና በምስጢር ስለመያዝ ... 5**

ፍቺዎች ... 5

መከላከያዎች ... 6

ስምምነት ... 6

የመጎብኘት/የመመልከት መብቶች ... 6

የጉብኝት ሬኮርድ ... 7

በወላጅ ጥያቄ መሠረት ሬኮርዶችን ማስተካከል ... 7

የመረጃ ድምሰሳ ሥርዓታዊ ክንዋኔ ... 7

የልጆች መብቶች ... 8

ሥነ ምግባራዊ መረጃ ... 8

**የአካለ ስንኩል ልጆች ሥነ-ምግባር ... 8**

ፍቺዎች ... 8

የትምህርት ቤት ባልደረቦች ሥልጣን ... 8

የገለጻ ውሳኔ ... 9

የምደባ ለውጥ ... 9

መሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት መስጫ ቦታ ... 10

የእርማት ይግባኝ/አቤቱታ ... 10

ልጁ ገና ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ... 10

ወደ ሕግ አስከባሪና የዳኝነት ባለሥልጣናት መተላለፍና የሚወሰድ እርምጃ ... 11

**ወላጆች በግለኝነት ልጆቻቸውን የግል ትምህርት ቤት ውስጥ በሕዝብ ወጪ ስለማስገባት ... 11**

በወጪዎች ማካካሻ ላይ ገደብ ... 11

**የወላጅነት መብትን አካለ-መጠን ለደረሱ ልጆች ማስተላለፍ ... 12**

**አለመግባባቶችን ስለመፍታት ... 13**

**ግልግል ... 13**

ግልግልን ለማበረታታት መገናኘት ........ 13

**በስቴት አቤቱታና በፍትህ ሂደት አቤቱታ መካከል ያለው ልዩነት ........ 14**

**የስቴት አቤቱታ ........ 14**

የስቴት አቤቱታን ስለመፍታት ........ 15
የፍትህ ሂደት አካል የሆነ የስቴት አቤቱታን ስለመፍታት ........ 15

**የፍትህ ሂደት አቤቱታ ........ 15**

የፍትህ ሂደቱ አቤቱታ ይዞታ ........ 16
ለፍትህ ሂደት አቤቱታው የሚሰጥ ምላሽ ........ 16
የማስታወቂያ ብቃት ........ 17
በፍትህ ሂደቶች ጊዜ የልጁ ሁኔታ/ቦታ ........ 17
ችግሩን የመፍታት ሂደት ........ 17
የ30 ቀን የጊዜ ሰሌዳው ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች ........ 18
የችግሩን መፍትሔ ስምምነት ........ 18
የፍትህ ሂደት ችሎት ........ 18
የአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ)፦ ........ 18
የፍትህ ሂደት አቤቱታ ርእስ ........ 19
የይግባኝ መብቶች ........ 19
በግልጽ ስለማውጣት ተጨማሪ መረጃ ........ 19
የወላጅ መብቶች ........ 19
የይግባኝ ውሳኔ ........ 19
ለብቻው የተለየ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ........ 20
የጊዜ ሰሌዳዎችና የችሎት አመቺነት ........ 20
የተፋጠኑ የጊዜ ሰሌዳዎች ........ 20
የፍርድ መጨረሻነት ........ 20

**ይግባኝ ........ 20**

***የጠበቆች ክፍያዎች ........ 21***

***የተያያዘ ........ 23***

# የሥርዓት መከላከያዎች

***የሥርዓት መከላከያ ማስታወቂያ በቀላሉ ለመረዳት በሚቻልበት መንገድና በትውልድ ቋንቋዎ የተጻፈ ሲሆን የመብቶችዎን ሙሉ ማብራሪያ ያካትታል።***

በዚህ ሰነድ ውስጥ የተካተቱት መከላከያዎች IDEA 2004ን በተግባር ላይ በሚያውለው ለአካለ ስንኩላን ግለሰቦች በወጣው ይትምህርት ማሻሻያ ድግጋጌ 2004 (IDEA 2004) 20 U.S.C. §1400 እና ሌሎችም እና COMAR 13A.05.01.01-.16 እና COMAR 13A.08.03 አማካኝነት የተመሠረተ ነው። እያንዳንዱ የሕዝብ ድርጅት የIDEA 2004 መስፈርቶችን የሚያሟሉ የሥርዓት መከላከያዎችን ይመሠርታል፣ ይጠብቃል እንዲሁም ሥራ ላይ ያውላል። የሥርዓት መከላከያ ሰነድ ቅጂ ለወላጆች በዓመት አንድ ጊዜ ይሰጣል፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች ጊዜ የሕዝብ ድርጅት ለወላጆች ሌላ የሰነዱን ቅጂ ይሰጣል፦

- በመጀመሪያ የመተላለፍ ወቅት ወይም የግምገማ ጥያቄ በወላጅ ሲቀርብ፣
- በትምህርት ዘመን ጊዜ ከአንቀጽ 34 CFR 300.151 እስከ 300.153 ሥር በተመለከተው መሠረት የመጀመሪያ የልዩ ትምህርት የስቴት አቤቱታ በቀረበበት ጊዜ፣
- በትምህርት ዘመን ጊዜ በአንቀጽ 34 C.F.R. §300.507 ሥር በተመለከተው መሠረት የመጀመሪያ የፍትህ ሂደት አቤቱታ በቀረበበት ጊዜ፣
- የቅጣት ክትትል ለማድረግ በተወሰነ ጊዜ እና
- በወላጅ ሲጠየቅ።

አንድ የሕዝብ ድርጅት ዌብ ሳይት ካለው ወቅታዊ የሆነውን የሥርዓት መከላከያዎችን ማስታወቂያ ቅጂ በኢንተርኔት ዌብ ሳይቱ ላይ ሊያወጣ ይችላል።

የሥርዓት መከላከያ ሰነድ የወላጆችን መብቶች ሙሉ ማብራሪያ የሚያካትት ሲሆን በቀላሉ ለመረዳት በሚቻልበት መንገድና ይህን ማድረግ በግልጽ የማይቻል ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በወላጅ የትውልድ ቋንቋ የተጻፈ ነው። የትውልድ ቋንቋው ወይም ሌላው የመግባቢያ ዘዴ በጽሑፍ የሚገለጽ ካልሆነ የሕዝብ ድርጅቱ የሥርዓት መከላከያዎቹ በቃል ወይም በሌላ አመቺ መንገድ ወደ ወላጁ የትውልድ ቋንቋ ወይም ሌላ የመግባቢያ ዘዴ መተርጎማቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል። የሕዝብ ድርጅቱ ማስታወቂያው በአግባቡ መተርጎሙንና ወላጆችም በአግባቡ የተረዱት መሆኑን የሚያረጋግጥ የጽሑፍ ማስረጃ ማስቀመጥ አለበት።

## የትውልድ ቋንቋ

***ወላጆች እነሱ በሚረዱት ቋንቋ መረጃ የማግኘት መብት አላቸው።***

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታው ጥቂት ከሆነ ግለሰብ ጋር በሚጠቀሙበት ጊዜ የትውልድ ቋንቋ ማለት የሚከተሉትን ነው፦

- ይህ ሰው ብዙውን ጊዜ የሚጠቀምበት ቋንቋ ወይም ልጅም ከሆነ የልጁ ወላጆች ብዙውን ጊዜ የሚጠቀሙበት ቋንቋ፣

- ከልጁ ጋር በቀጥታ በሚገናኙበት ጊዜ ሁሉ (የልጁን ግምገማም ጨምሮ) ልጁ በቤቱ ውስጥ ወይም በሚማርበት አካባቢ ብዙውን ጊዜ የሚጠቀምበት ቋንቋ።

መስማት የሚሳነው ወይም አይነ ስውር የሆነ ሰው፣ ወይም የጽሑፍ ቋንቋ የሌለው ሰው ከሆነ የመግባቢያ ዘዴው ይህ ሰው ብዙውን ጊዜ የሚጠቀምበት ዘዴ መሆን አለበት (መስማት የሚሳናቸው ሰዎች የሚጠቀሙበት የምልክት ቋንቋ፣ የአይነ ስውራን ሥርዓተ ጽሕፈት ወይም የቃል ንግግር)።

## ኢሜል

***አማራጩ ካለ ወላጆች ማስታወቂያዎች በኢሜል እንዲደርሳቸው ማድረግ ይችላሉ።***

አንድ የሕዝብ ድርጅት ወላጆች ሰነዶች በኢሜል እንዲደርሳቸው አማራጭ የሚሰጥ ከሆነ የሚከተሉት በኢሜል እንዲደርስዎት ማድረግ ይችላሉ፦

- የቅድሚያ ማስታወቂያ፣
- የሥርዓት መከላከያ ማስታወቂያ፣ <u>እና</u>
- የፍትህ ሂደትን የሚመለከቱ ማስታወቂያዎች።

## ቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ

***ወላጆች አንድ የሕዝብ ድርጅት የልጃቸውን ልዩ ትምህርት ጉዳይ በተመለከተ የሚያደርጋቸውን ድርጊቶች በጽሑፍ የማግኘት መብት አላቸው።***

### ማስታወቂያ

አንድ የሕዝብ ድርጅት የሚከተሉትን ባደረገ ቁጥር ለወላጆች የጽሑፍ ማስታወቂያ መስጠት አለበት፦

- የአንድን ልጅ የማንነት መለያ፣ ግምገማ፣ የትምህርት መርሀ-ግብር ወይም የትምህርት ምደባን ወይም ለልጁ የሚሆን የ ነጻ አግባቢነት ያለው ሕዝባዊ ትምህርት (FAPE) አቅርቦትን አስመልክቶ አነሳሽነት ወይም ለውጥ ለማድረግ ሐሳብ ሲያቀርብ፣ ወይም
- የአንድን ልጅ የማንነት መለያ፣ ግምገማ፣ የትምህርት መርሀ-ግብር ወይም የትምህርት ምደባን ወይም ለልጁ የFAPE አቅርቦትን አስመልክቶ አነሳሽነት ወይም ለውጥ ለማድረግ ሐሳብ ሲቃወም።

አንድ የጽሑፍ ማስታወቂያ የወላጅ ፍቃድ የሚያስፈልገው ከሆነ የሕዝብ ድርጅቱ የጽሑፍ ማስታወቂያ አብሮ አንድ ላይ ሊሰጥ ይችላል።

### የጽሑፍ ማስታወቂያ ይዞታ

ይህ የጽሑፍ ማስታወቂያ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፦

- የሕዝብ ድርጅቱ ያነሳሳው/ያነሳሳቸው ወይም ውድቅ ያደረገው/ያደረጋቸው ድርጊት/ቶች ማብራሪያ መስጠት፣
- የሕዝብ ድርጅቱ ድርጊቱን/ድርጊቶቹን ለመፈጸም ወይም ለመቃወም ምን እንዳነሳሳው የሚገልጽ ማብራሪያ፣
- የሕዝብ ድርጅቱ ድርጊቱን/ድርጊቶቹን ለመፈጸም ወይም ለመቃወም የወሰነበትን እያንዳንዱን የግምገማ ሂደት፣ ቴስት፣ መዝገብ ወይም ሪፖርት የሚያብራራ መግለጫ፣
- ወላጆች IDEA ውስጥ በሚገኝ የሥርዓት መከላከያ አቅርቦት መሠረት መብቶች እንዳላቸው የሚገልጽ መግለጫ፣
- የሕዝብ ድርጅቱ የሚፈጽመው ወይም የሚቃወመው ድርጊት ለግምገማ የሚተላለፍ የመጀመሪያ ድርጊት ካልሆነ ወላጆች የሥርዓት መከላከያ ቅጂ የሚያገኙበትን መንገድ መናገር፣
- ወላጆች IDEA ን ለመረዳት እርዳታ የሚያገኙባቸውን ምንጮች ማካተት፣
- የልጁ የግል የትምህርት መርሀ-ግብር (IEP) ቡድን ያያቸውን አማራጮች ማብራራትና በምርጫዎቹ ተቃውመው የተተውበትን ምክንያቶች መንገር፣ <u>እንዲሁም</u>
- የሕዝብ ድርጅቱ ድርጊቱን ለመፈጸም ወይም ለመቃወም የተጠቀመባቸውን ምክንያቶች ማብራሪያ ማቅረብ።

## ስምምነት

***አንድ የሕዝብ ድርጅት አንድን ልጅ የልዩ ትምህርት ግምገማና ተዛማጅ አገልግሎቶች ለመስጠት ሲፈልግና ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ከማቅረቡ በፊት የወላጅ ስምምነት ማግኘት አለበት።  ወላጆች ስምምነቱን መልሰው የመውሰድ መብት አላቸው። ለግምገማ ስምምነት ከማግኘት የተገለሉ አንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች አሉ።***

ስምምነት ማለት ወላጆች፦

- ስምምነቱን ለመስጠት ስለተጠየቀበት ድርጊትና ተዛማጅ መረጃ በትውልድ ቋንቋቸው ወይም ሌላ መግባቢያ ዘዴያቸው ሙሉ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፣
- ስምምነታቸው የተጠየቀበትን ሁኔታ በሚገባ ተረድተውትና መስማማታቸውንም በጽሑፍ ያረጋገጡ ሲሆን፣ ስምምነቱም ለሚመለከተው ሁሉ ሊተላለፍ የሚችልበትን ሁኔታ የሚገልጽና የነዚሁኑም ሬኮርዶች አካል የሆነውን ዝርዝር የሚያካትት መሆኑን ተገንዝበዋል፣ እና
- ስምምነት መስጠት በወላጆች ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ መሆኑንና ሲፈልጉም በማንኛውም ጊዜ ስምምነታቸውን ሊሽሩት ወይም ሊሰርዙት የሚችሉ መሆናቸውን ተረድተዋል ማለት ነው።

ወላጆች የሰጡትን ስምምነት ቢሽሩ የሕዝብ ድርጅቱ ስምምነቱ ከደረሰው ጊዜና ስምምነቱ ከመሻሩ መሃል ባለው ጊዜ ውስጥ የተከሰተን ድርጊት አይሰርዝም።

## የመጀመሪያውን ግምገማ ለማድረግ የወላጅ ስምምነት

አንድ የሕዝብ ድርጅት አንድ ልጅ ለልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎች ብቁ መሆኑን የመጀመሪያ ግምገማ ከማድረጉ በፊት የሕዝብ ድርጅቱ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፦

- ለወላጆች ስለ ድርጊቱ አቅርቦት በጽሑፍ የቅድምያ ማስታወቂያ መስጠት፣ **እንዲሁም**
- የወላጅ ስምምነት ማግኘት።

የሕዝብ ድርጅቱ የአንድ ልጅ አካለስንኩልነት ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ያስፈልገዋል ብሎ ለመወሰን የሚያስፈልገውን ግምገማ ለማድረግ ተረድተው የሰጡትን ስምምነት ለማግኘት ተገቢ ጥረት ማድረግ አለበት።

አንድ ወላጅ ለመጀመሪያ ግምገማ ስምምነት ሰጠ ማለት የሕዝብ ድርጅቱ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ለልጁ መስጠት እንዲጀምርም ስምምነት ሰጠ ማለት አይደለም።

## በመንግሥት አሳዳጊነት ሥር ላሉ የመጀመሪያ ግምገማ ለመስጠት ያሉ ልዩ ሕጎች

አንድ ልጅ በመንግሥት አሳዳጊነት ሥር ያለ ከሆነና ከወላጆቹ ጋር የማይኖር ከሆነ፣ ልጁ አካለስንኩል መሆኑን የመጀመሪያ ግምገማ ለማድረግ የሕዝብ ድርጅቱ የወላጅ ስምምነት የማያስፈልገው የሚከተሉት የተሟሉ ከሆነ ነው፦

- ምንም እንኳን በቂ ጥረት ቢያደርግም፣ የሕዝብ ድርጅቱ የልጁን ወላጅ ማግኘት አልቻለም፣
- በስቴቱ ሕግ መሠረት የወላጆች የወላጅነት መብት ተገፍፏል፣ **ወይም**
- አንድ ወላጅ በትምህርት ነክ ውሳኔዎችና ለመጀመሪይ ግምገማ ስምምነት የመስጠት መብቱ በዳኛ ፍርድ አማካኝነት ተገፍፎ ለሌላ ሰው ተሰጥቶ ከሆነ።

## ለአገልግሎቶች የወላጅ ስምምነት

አንድ የሕዝብ ድርጅት ለአንድ ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ከመስጠቱ በፊት ተረድተው የሰጡት ስምምነት ለማግኘት ተገቢ ጥረቶች ማድረግ አለበት።

ወላጆቹ የሚከተሉትን ካደረጉ የሕዝብ ድርጅቱ የግልግል ወይም የፍትህ ሂደቶችን ተጠቅሞ ስምምነት ማግኘት ወይም የልጁ ወላጆች ስምምነት ሳይሰጡ የልጁ የIEP ቡድን በሰጠው ምክር መሠረት ልጁ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲያገኝ ፍርድ መጠቀም **የለበትም፣**

- ልጃቸው ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲያገኝ ስምምነት አልሰጥም ካሉ፣ ወይም
- ለመጀመሪያ ጊዜ ልጁ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲያገኝ ስምምነት እንዲሰጡ ተጠይቀው መልስ ሳይሰጡ ከቀሩ።

ወላጆች ልጃቸው ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲያገኝ የመጀመሪያ ስምምነት አልሰጥም ካሉ፣ ወይም ወላጆች ስምምነት እንዲሰጡ ተጠይቀው መልስ ሳይሰጡ ከቀሩ፣ የሕዝብ ድርጅቱ፦

- የነጻ ተገቢ ሕዝባዊ ትምህርት (FAPE) ለልጃቸው እንዲኖር ማድረግ ያለባቸውን ግዴታ ሕግ አልጣሱም፣ **እንዲሁም**
- ለልጃቸው የግል የትምህርት መርሀ-ግብር (IEP) ስብሰባ የማድረግ ወይም ለልጃቸው IEP የማዳበር ግዴታ የለበትም።

## ለዳግም ግምገማዎች የወላጅ ስምምነት

የሕዝብ ድርጅቱ አዲስ የግል ግምገማዎች ለልጁ ከማኪያሄዱ በፊት፣ የሕዝብ ድርጅቱ የሚከተሉትን በግልጽ ካላሳየ በስተቀር ተረድተው የሰጡትን ስምምነት ማግኘት አለበት፦

- ዳግም ግምገማ ለማድረግ የወላጅ ስምምነት ለማግኘት ተገቢ ጥረቶች አድርጎ ነበር፣ **እና**
- ወላጁ መልስ አልሰጠም።

አዲስ ግምገማዎች ለማድረግ ወላጆች ስምምነት አልሰጥም ካሉ፣ የሕዝብ ድርጅቱ በሽምግልና የሚደረግ ግልግልና የፍትህ ሂደትን ተጠቅሞ የወላጆችን እምቢታ የማስሻር መብት ያለው ሲሆን ግዴታው ግን አይደለም። ልክ እንደ መጀመሪያ ግምገማው፣ የሕዝብ ድርጅቱ አዲስ ግምገማዎች አላደርግም ቢል በIDEA ሥር ያሉበትን ግዴታዎች አልጣሰም።

**<u>የወላጅ ስምምነትን ለማግኘት የተደረጉ ተገቢ ጥረቶችን መመዝገብ</u>**

አንድ የሕዝብ ድርጅት ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመስጠት፣ ዳግም ግምገማ ለማድረግና በመንግሥት አሳዳጊነት ሥር ያሉ የልጆችን ወላጆች የመጀመሪያ ግምገማ ለማድረግ ስምምነት ለማግኘት ያደረጋቸውን ተገቢ ጥረቶች መዝግቦ በሰነድ መያዝ አለበት።

ሰነዱ የሕዝብ ድርጅቱ የወላጅ ስምምነት ለማግኘት ያደረጋቸውን የሚከተሉት ዓይነት ሙከራዎች ሬኮርድ ማካተት አለበት፦

- የተደወሉና የተሞከሩ የስልክ ጥሪዎች ዝርዝርና ውጤታቸው፣
- ለወላጆች የተላኩ የደብዳቤ ግልባጮችና ምንም ዓይነት ምላሾች፣ **<u>እንዲሁም</u>**
- የወላጅ ቤት ወይም ሥራ ላይ የተደረጉ ጉብኝቶች የዝርዝር ሬኮርዶችና ውጤታቸው።

**<u>ሌሎች ለስምምነት መሟላት ያለባቸው ነጥቦች</u>**

የወላጅ ስምምነት በሕዝብ ድርጅት ፊት መቅረብ አስፈላጊ **<u>ያልሆነባቸው</u>** ግዜዎች፦

- የልጅዎን ግምገማ ወይም ዳግም ግምገማ ለማድረግ ዷሪ መረጃን ሲገመግሙ፣ **<u>ወይም</u>**
- ለሁሉም ልጆች የሚሰጥ ፈተና ወይም ሌላ ግምገማ ለልጅዎ ሲሰጥ፣ ከልጆቹ ወላጆች ሁሉ ፈተናው ወይም ግምገማው ከመሰጠቱ በፊት ስምምነት የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር።

የሕዝብ ድርጅቱ ወላጅ ለአንድ አገልግሎት ወይም ድርጊት ስምምነት አልሰጥም ያለበትን እምቢታ ተጠቅሞ ወላጁን ወይም ልጁን ከሌላ አገልግሎት፣ ጥቅማጥቅም ወይም ድርጊት መከልከል አይችልም።

አንድ ወላጅ ልጃቸውን የግል ትምህርት ቤት ውስጥ በራሱ ወጪ ቢያስመዘግብ፣ የሚከተሉት ከተከሰቱ የሕዝብ ድርጅቱ በሽምግልና የሚደረግ ግልግልን ወይም የፍትህ ሂደትን ተጠቅሞ የልጁን ብቃት መገምገም አይችልም እንዲሁም ልጁ ተገቢ አገልግሎቶች እንዲያገኝ የማድረግ ግዴታ የለበትም፦ ብቃት አለው

- ወላጁ ልጁ የመጀመሪያ ግምገማ ወይም ዳግም ግምገማ እንዲያገኝ ስምምነት አልሰጠም፣ **<u>ወይም</u>**
- ወላጁ ስምምነት እንዲሰጥ ተጠይቆ መልስ ካልሰጠ።

## በግል የሚደረግ የትምህርት ግምገማ

***አንድ ወላጅ የሕዝብ ድርጅት በፈጸመው ግምገማ የማይስማማ ከሆነ፣ ወላጁ ለሕዝብ ድርጅቱ በማይሠራ ሰው ልጁን የማስገምገም መብት አለው። .***

**<u>ፍቺዎች</u>**

- በግል የሚደረግ የትምህርት ግምገማ ማለት፣ የልጁ ትምህርት ኃላፊነት ላለበት የሕዝብ ድርጅት ተቀጥሮ የማይሠራ፣ ሌላ ብቁ ሠራተኛ ያደረጋቸው ቴስቶችና የግምገማ ሂደቶች ናቸው።

- የሕዝብ ወጪ ማለት የሕዝብ ድርጅቱ የግምገማ ወጪውን በሙሉ ይከፍላል ወይም ግምገማው የሚሰጠው በወላጆች ወጪ እንዳይሆን ያረጋግጣል።

ከዚህ በታች ባሉት ሂደቶች መሠረት ወላጆች ለልጃቸው በIDEA ሥር ለልጃቸው በግል የሚሰጥ የትምህርት ግምገማ የማግኘት መብት አላቸው። የሕዝብ ድርጅቱ የግል ግምገማ ጥያቄ በቀረበለት ጊዜ፣ ለወላጆቹ ስለሚከተሉት ነጥቦች መረጃ ይሰጣል፦

- በግል የሚሰጥ የትምህርት ግምገማ የት ሊገኝ እንደሚችል፤ **<u>እንዲሁም</u>**
- ስለ ግል የትምህርት ግምገማ የሕዝብ ድርጅቱ ያለውን መመዘኛዎች።

**<u>የሕዝብ ድርጅት መመዘኛዎች</u>**

አንድ የግል የትምህርት ግምገማ በሕዝብ ወጪ የሚደረግ ከሆነ፣ የግል የትምህርት ግምገማውን ለማግኘት የሚጠቀምባቸ መመዘኛዎች፣ ግምገማው የሚሰጥበት ቦታና የፈታኙን ብቃት ጨምሮ፣ የሕዝብ ድርጅቱ ራሱ ግምገማን ሲያካሳ ከሚጠቀምባቸው መመዘኛዎች ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለበት፣ እነዚህ መመዘኛዎች ወላጁ የግል የትምህርት ግምገማ የማግኘት መብቱ ጋር አብረው መሄድ አለባቸው። ከዚህ በላይ ከተገለጹት መመዘኛዎች በስተቀር በሕዝብ ወጪ የሚደረግ የግል የትምህርት ግምገማ ከማግኘት ጋር በተያያዘ የሕዝብ ድርጅቱ የቅድመ-ሁኔታዎችና የጊዜ ገደቦች ጫና መፍጠር አይችልም።

### በሕዝብ ወጪ የሚደረግ ግምገማ ጋር የተያያዘ የወላጅ መብት

ወላጆች የሕዝብ ድርጅት በሰጠው ግምገማ የማይስማሙ ከሆነ በሕዝብ ወጪ የሚደረግ የግል ትምህርታዊ ግምገማ የማግኘት መብት አላቸው። ወላጆች የግል ትምህርታዊ ግምገማ በሕዝብ ወጪ እንዲደረግላቸው ጥያቄ ካቀረቡ፣ የሕዝብ ድርጅቱ አላስፈላጊ መዘግየት ሳያደርግ ከሚከተሉት አንዱን የማድረግ ግዴታ አለበት፦

- ግምገማው ተገቢ መሆኑን ለማሳየት የፍትህ ሂደት እንዲደረግ ማነሳሳት፣ ወይም
- የሕዝብ ድርጅቱ በችሎት ፊት ቀርቦ ወላጆቹ ያገኙት ግምገማ የሕዝብ ድርጅቱን መመዘኛዎች የማያሟላ እንደሆነ በግልጽ ካላሳየ በስተቀር፣ የግል ትምህርታዊ ግምገማ በሕዝብ ወጪ መሰጠቱን ማረጋገጥ።

የሕዝብ ድርጅቱ የፍትህ ሂደት አነሳስቶ ፍርዱ የሕዝብ ድርጅቱ ግምገማ ተገቢ ነው የሚል ከሆነ፣ ወላጆች በግል የሚሰጥ ይትምህርት ግምገማ የማግኘት መብታቸው አሁንም የተጠበቀ ቢሆንም በሕዝብ ወጪ ግን ሊሆን አይችልም።

ወላጆች የግል ትምህርታዊ ግምገማ እንዲደረግላቸው ጥያቄ ካቀረቡ፣ የሕዝብ ድርጅቱ የሕዝብ ግምገማውን ወላጆች የተቃወሙበትን ምክንያት ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም የወላጅ ማስረጃ አስፈላጊ አይደለም፣ የሕዝብ ድርጅቱም በሕዝብ ወጪ የሚደረገውን የግል ትምህርታዊ ግምገማ ለማቅረብ ወይም የሕዝብ ድርጅቱን ግምገማ በችሎት ፊት ቀርቦ ለማስረዳት አነሳሽነት ለመውሰድ አላስፈላጊ መዘግየት ማሳየት የለበትም።

### በወላጅ አነሳሽነት የሚደረግ ግምገማ

ወላጆች ምንጊዜም ቢሆን የግል ትምህርታዊ ግምገማን፣ እራሳቸው በግላቸው ከሚመርጡት የሰለጠነ ባለሙያ በራሳቸው ወጪ የማግኘት መብት አላቸው። የ IEP ቡድኑም፣ ለልጁ መቅረብ በሚገባው FAPE ላይ ውሳኔ በሚያስተላልፍበት ወቅት፣ በወላጆች አነሳሽነት፣ በወላጆች የግል ወጪ፣ ከተደረገው ግምገማ የተገኘውን መረጃ፣ ግምገማው የሕዝብ ድርጅቱን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ፣ ማጤን ይኖርበታል። እንደዚሁም ደግሞ፣ በወላጆች የግል አነሳሽነት የተደረገው የግል የግምገማ ውጤት የተጠቃሹን ልጅ ጉዳይ በሚመለከት የፍትህ ሂደት ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል።

### ግምገማ በአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ) እንዲደረግ ስለመጠየቅ

አንድ የአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ) ከአስተዳደር ችሎት ቢሮ (OAH) ጋር አብሮ በመሆን አንድ ይግል ትምህርታዊ ግምገማ በችሎት ላይ የሚሰማ ጉዳይ አካል ሆኖ እንዲቀርብ ከጠየቀ፣ ግምገማው የሚካሄደው በሕዝብ ወጪ መሆን ይኖርበታል።

## መረጃን በግልና በምስጢር ስለመያዝ

***ወላጆች የልጃቸውን ሬኮርዶች የማየትና ሬኮርዱ ስህተት አለው ብለው ካሰቡ የሕዝብ ድርጅቱ ሬኮርዱን እንዲያስተካክል የመጠየቅ መብት አላቸው። ወላጆች የልጃቸውን መረጃ በተመለከተ በግልጽ ለማሳየት ስምምነት የመስጠት መብት ያላቸው ሲሆን፣ ስምምነት መስጠት የማያስፈልግባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። ወላጆች የልጃቸውን ትምህርታዊ ሬኮርዶች የሕዝብ ድርጅቱ በግልና በምስጢር ይይዝልኛል ብሎ የመጠበቅና የልጃቸው ትምህርታዊ መረጃ አላስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከጥቅም ውጪ ሲሆን እንዲደመሰስላቸው የሕዝብ ድርጅቱን የመጠየቅ መብት አላቸው።***

### ፍቺዎች

ድምሰሳ ማለት፣ የአንድን ግለሰብ ማንነት ለመለየት ያስችሉ የነበሩ ማንኛቸውም ዓይነት ግለሰባዊ መለያዎች ከእንግዲህ ወዲያ ፈጽሞ ሊታወቁ እንዳይችሉ አድርጎ መደምሰስ ወይም ማጥፋት ማለት ነው።

የትምህርት ሬኮርዶች ማለት፣ “የትምህርት ሬኮርዶች” በሚለው 34 C.F.R. ክፍል 99 ፍቺ (የቤተሰብ የትምህርት መብትና የመረጃው ምስጢራዊነት [FERPA] የ1974 ድንጋጌ) ሥር የተመለከቱ ሬኮርዶች ማለት ነው።

ተሳታፊ ድርጅት ማለት፣ በ IDEA ክፍል B ሥር በተመለከተው መሠረት፣ የግለሰባዊ መለያ መረጃዎችን የሚሰበስብ፣ አጠናቅሮ የሚይዝ፣ ወይም የሚጠቀም፣ ወይም እነዚህን መረጃዎች ለማግኘት የሚቻልበት ማንኛውም ድርጅት ወይም ተቋም ማለት ነው።

ግለሰባዊ መለያ መረጃዎችም የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፦

- የልጅ ስም፣ የወላጆች ስም፣ ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል ስም፣
- የልጁ መኖሪያ አድራሻ፣
- ግለሰባዊ መለያ፣ ለምሳሌ የልጁ ሶሻል ሴክዩሪቲ ቁጥር፣ ወይም

- የልጁን ማንነት በሚዛናዊ እርግጠኝነት ለመለየት የሚያስችሉ የግለሰባዊ መግለጫዎች ዝርዝር ወይም ሌሎች መረጃዎች።

## መከላከያዎች

እያንዳንዱ ተሳታፊ ድርጅት፣ የግለሰቦችን ግላዊ መለያ መረጃዎችን ሲሰበስብ፣ አጠናቅሮ ሲያስቀምጥ፣ ለሌሎችም ሲያስተላልፍ፣ መረጃዎቹንም ሲደመስስ/ሲያጠፋቸው፣ ምስጢራዊነታቸውን በጥንቃቄ ይጠብቃል። የግላዊ መለያ መረጃዎችን በጥንቃቄ ለመጠበቅ እንዲያስችለውም፣ የሕዝብ ድርጅቱ ከድርጅቱ አንዱን ባለሥልጣን በዚህ ሥራ በኃላፊነት ላይ ይመድባል። ከነዚህ የመከላከያ ሥርዓቶች መሰናዶዎች በተጨማሪም፣ የፌዴራላዊና ክፍለ ግዛታዊ ሕጎችና ደንቦችም እንደዚሁ የትምህርት ሬኮርዶችን ደህንነት መጠበቅን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ያደርጋሉ። ለግለሰባዊ መለያነት የሚያገለግሉ መረጃዎችን የሚሰበስቡ፣ ወይም መረጃዎቹን የሚጠቀሙ፣ የሕዝብ ድርጅቱ ሠራተኞች የሆኑ ሁሉ፣ እነዚህን የግል መለያ መረጃዎችን ጥብቅ ምስጢራዊነት ለመጠበቅ የግዛታዊ ፖሊሲዎችንና አፈጻጸማዊ ሂደታቸውን አስመልክቶ ተገቢውን ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል። እያንዳንዱ ተሳታፊ ድርጅት፣ ለሕዝብ ቁጥጥር በሚያመች መልኩ፣ ለግለሰባዊ መለያነት ከሚያገለግሉ መረጃዎች ጋር ግንኙነት የሚኖራቸውን ሠራተኞቻቸውን ስምና የሥራ ኃላፊነት ዝርዝር በግልጽ መዝግበው ያስቀምጣሉ።

## ስምምነት

በ IDEA ሥር በተደነገገው መሠረት፣ የግለሰባዊ መለያ መረጃዎችን የሚሰበስቡና የሚጠቀሙ የተሳታፊ ድርጅቶች ኦፊሴላዊ (የታወቁ) ሠራተኞች ውጪ፣ ወይም በ IDEA ሥር በተመለከተው መሠረት የአንድን አካለ ስንኩል ተማሪ የ FAPE ፍላጎቶችን ማጤንና ማሟላትን ከሚመለከት ውጪ በሆነ መልኩ፣ የግላዊ መለያ መረጃዎችን ይፋ ከማድረጋቸው በፊት የወላጆችን የስምምነት ፈቃድ ማግኘት ይጠበቅባቸዋል። አንድን ልጅ ወደ ሕግ ፊት ማቅረብንና በአንድ አካለ ጎዶሎ ተማሪ በተፈጸመ የወንጀል ድርጊት ሪፖርት መሠረት፣ በሕግ አስከባሪዎችና በዳኝነት ባለስልጣናት የሚወሰድ እርምጃን በተመለከተም፣ ሪፖርቱን የማስተላለፉ ጉዳይ በ FERPA የተፈቀደ እስከሆነ ድረስ፣ የወላጅ ፈቃድን መጠበቅ የግድ አይሆንም።

በ FERPA ሥር የተፈቀደ እስካልሆነ ድረስ፣ አንድ የትምህርት ድርጅት ወይም ተቋም፣ ከወላጅ ስምምነት ውጪ የግለሰባዊ መለያ መረጃን ከትምህርት ሬኮርዱ ውስጥ በማውጣት ለተሳታፊ ድርጅቶች ሊሰጥ አይችልም። መንግሥት ያወጣቸው ፖሊሲዎችና ሥርዓታዊ መመሪያዎች፣ ምስጢራዊነትን መጠበቅን ጨምሮ፣ በ IDEA ና FERPA መሠረት መከበራቸውን ለማረጋገጥ፣ የሚጠቀምባቸውን ቅጣቶች ጨምሮ፣ MSDE ለሕዝብ ድርጅቶች ሥርዓታዊ መመሪያዎችን ነድፎ አዘጋጅቷል።

እያንዳንዱ የሕዝብ ድርጅት፣ የግለሰባዊ መለያ መረጃዎችን ምስጢራዊ አጠባበቅ በተመለከተ ወላጆች የተሟላ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣ ማስታወቂያዎቹ ለወላጆች የቱን ያክል በበቂ ሁኔታ መዳረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉት ዝግጁ ሥርዓታዊ መመሪያዎች ሊኖሩት ይገባል። ይህም ከዚህ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

- ማስታወቂያው በክፍለ ግዛቱ ውስጥ ለሚኖሩት የተለያዩ ማህበረሰቦች በትውልድ ቋንቋቸው ተዘጋጅቶ የቱን ያክል እንደተሰራጨ የሚያሳይ መግለጫ፣
- የግል መለያዎቻቸው ተመዝግቦ የተያዘላቸው ልጆችና የተጠየቁ ተጨማሪ መረጃዎች፣
- ተሳታፊ ድርጅቶች የግለሰባዊ መለያ መረጃዎችን በአግባቡ ማስቀመጥን፣ ለሌላ ሶስተኛ ወገን መስጠትን፣ ጠብቆ ማቆየትንና መደምሰስን በተመለከተ ሊከተሏቸው የሚገቡ ፖሊሲዎችና ሥርዓታዊ መመሪያዎችን የሚያመለክት አጭር የማጠቃለያ መግለጫ፣
- ወላጅ ስምምነቱን ለመስጠት ፈቃደኛ ባልሆነበት አጋጣሚ ድርጅቱ የተጠቀመባቸውን ፖሊሲዎችና ሥርዓታዊ መመሪያዎች የሚያሳይ መግለጫ፣ እና
- በ FERPA ና ደንቦችን ለማስፈጸም በሚለው በ34 C.F.R. §99 ሥር የተመለከቱትን ጨምሮ፣ ይህን መረጃ በተመለከተ ወላጆችና ልጆች የሚኖራቸውን መብቶች የሚገልጽ።

ከማንኛውም ዓይነተኛ መለያ፣ ከቦታና ከግምገማ እንቅስቃሴ ቀደም ብሎ ማስታወቂያው መታተም፣ ወይም በጋዜጦች፣ ወይም በሌሎች የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ሁሉ በበቂ ስርጭት ለሕዝብ እንዲዳረስ ሆኖ መታወጅ ይኖርበታል።

## የመጎብኘት/የመመልከት መብቶች

እያንዳንዱ የሕዝብ ድርጅት ወላጆች ልጃቸውን በሚመለከት የተሰበሰቡ፣ ተጠናቅረው የተያዙ፣ ወይም ድርጅቱ የልጁን ማንነት መለያ፣ ግምገማና የትምህርት ምደባ፣ እንደዚሁም የልጁን የ FAPE አቅርቦት አስመልክቶ የሚጠቀምባቸውን መረጃዎች ሁሉ አይተው እንዲመረምሩና ካስፈለገም እንዲያስተካክሉ/እንዲከልሱ ይፈቅዳል። ድርጅቱ ካለምንም አላስፈላጊ የጊዜ ማጓተት፣ ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ሁሉ ምላሽ መስጠትንና IEPን በተመለከተ ከሚደረግ ስብሰባ በፊት፣ ወይም ማንኛውም የፍትህ ሂደትን የሚመለከት ሸንጎ ከመሰየሙ በፊት፣ እንደዚሁም ጥያቄው ከቀረበ ከ45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠትን ማክበር ይኖርበታል።

በዚህ ክፍል ሥር የሚጠቀሱ የትምህርት ሬኮርዶችን የመመርመርና የመከለስ የወላጅ መብቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- ሬኮርዶችን በሚመለከት ለሚቀርቡ ሚዛናዊ የማብራሪያና የትርጓሜ ጥያቄዎች ከተሳታፊ ድርጅቱ የሚሰጥ ምላሽ፣
- የሬኮርድ ቅጂዎችን ለወላጆች አለመስጠት ወላጆች ሬኮርዶችን አይተው ለመመርመርና ለመከለስ እንዳይችሉ መሠረታዊ መብቶቻቸውን አጥብቆ የሚጋፋ በመሆኑ፣ ድርጅቱ የሬኮርድ ቅጂዎች ለወላጆች እንዲሰጥ ለመጠየቅ፣ እና
- ወላጆች ሬኮርዶችን የሚመረምርና የሚከልስ ተወካይ እንዲኖራቸው ለማድረግ።

የሕዝብ ድርጅቱ እንደ አሳዳጊነት፣ መለያየት እና ከትዳር መፋታት የመሳሰሉትን ጉዳዮች አስተናጋጅ (ገዢ) በሆነው የክፍለ ግዛቱ ተግባራዊ ሕግ ሥር በተመለከተው መሠረት፣ ወላጆች በጉዳዩ ላይ ስልጣን እንደሌላቸው ካልተነገረው በስተቀር፣ ድርጅቱ ወላጆች ከልጃቸው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሬኮርዶች ለመመርመርና ለመከለስ ስልጣኑ እንዳላቸው አድርጎ ለገምት ይችላል።

## የጉብኝት ሬኮርድ

እያንዳንዱ የሕዝብ ድርጅት፣ ከወላጆችና አግባብነት ካላቸው ወይም ስልጣኑ ካላቸው የሕዝብ ድርጅት ሠራተኞች ውጪ፣ በ IDEA ክፍል B ሥር በተመለከተው መሠረት የተሰበሰቡ፣ ተጠናቅረው የተያዙ፣ ወይም በጥቅም ላይ የዋሉ የትምህርት ሬኮርዶችን ለማየት/ለመጎብኘት ዕድል ያገኙ ግለሰቦችን ስም፣ ግለሰቡ የጉብኝቱን ዕድል ያገኙበትን ቀንና ጉብኝቱ እንዲፈቀድለት ያስቻለውን ምክንያት/ዓላማ፣ በማካተት መዝገቦ ይይዛል። አንድ የትምህርት ሬኮርድ፣ ከአንድ በላይ ልጆችን ሬኮርድ አካትቶ የሚይዝ ከሆነ፣ ወላጆች ልጃቸውን የሚመለከተውን ሬኮርድ ብቻ ለይተው በማውጣት ነው የማየት፣ የመመርመርና የመከለስ መብት የሚኖራቸው፣ አለበለዚያም እነሱን የሚመለከተውን/የሚፈልጉት ሬኮርድ የትኛው እንደሆነ ተለይቶ ይነገራቸዋል። እያንዳንዱ የሕዝብ ድርጅት በድርጅቱ የተሰበሰቡ፣ ተጠናቅረው የተያዙ፣ ወይም በጥቅም ላይ የዋሉ የትምህርት ሬኮርዶችን ዓይነትና፣ የሬኮርዶቹ ክምችትም የሚገኝበትን ቦታ፣ ወላጆች ሲጠይቁ ይሰጣል። ወላጆች ሬኮርዶቹን ለመመርመርና ለመከለስ ያላቸውን መብት ከመጠቀም የሚያግዳቸው እስካልሆነ ድረስ፣ እያንዳንዱ የሕዝብ ድርጅት ለወላጆች ለሚደረጉ የትምህርት ሬኮርዶች ቅጂዎች ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል። አንድ የሕዝብ ድርጅት ከትምህርት ሬኮርዶች ውስጥ መረጃ ለመፈለግ ወይም ለማውጣት ክፍያ መጠየቅ አይችልም።

## በወላጅ ጥያቄ መሠረት ሬኮርዶችን ማስተካከል

በ IDEA ሥር በተመለከተው መሠረት የተሰበሰቡ፣ ተጠናቅረው የተያዙ፣ ወይም በጥቅም ላይ የዋሉ የትምህርት ሬኮርዶች ውስጥ ያለው መረጃ ትክክል አይደለም፣ ወይም አሳሳች ነው ወይም ምስጢራዊነትን ወይም ሌሎች የልጁት መብቶች ይጋፋል ብለው ባመኑ ጊዜ፣ ወላጆች መረጃው ይስተካከል ዘንድ መረጃውን የያዘውን የሕዝብ ድርጅት ሊጠይቁ ይችላሉ። የሕዝብ ድርጅቱም ጥያቄውን ከተቀበለበት ዕለት አንስቶ፣ በተመጣጣኝ ጊዜ ውስጥ፣ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት መረጃውን ያስተካክል እንደሆነ ይወስናል። የሕዝብ ድርጅቱ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት መረጃውን የማስተካከሉን ጥያቄ እንደማይቀበለው ከወሰነ፣ ይህንኑ እምቢታውን ለወላጆች ማሳወቅና፣ ወላጆችም የትምህርት ሬክኮርዶችን በተመለከተ ያነሱትን ጥያቄ እሸንጎ ፊት አቅርበው የመሞገት መብት እንዳላቸው ድርጅቱ ሊያሳውቃቸው ይገባል። የትምህርት ሬኮርዶች መረጃ ሙግትን የሚሰማው የፍትህ ሂደት ሸንጎ የሚከናወነው በ34 C.F.R. §99.22 ውስጥ በተመለከተው በ FERPA መሠረት መሆን አለበት።

የሕዝብ ድርጅቱ፣ በተጠየቀ ጊዜ፣ በትምህርት ሬኮርዶች ውስጥ የሚገኝ መረጃን በተመለከተ የተነሳው ሙግት ለሸንጎ ቀርቦ፣ እንደተባለው መረጃው ትክክለኛነት የጎደለው አለመሆኑን፣ አሳሳች አለመሆኑን፣ ወይም ምስጢራዊነትን ወይም ሌሎች የልጁን መብቶች የሚጻረር አለመሆኑን ለማረጋገጥ ይቻለው ዘንድ ለሸንጎ እንዲቀርብ ዕድል ይሰጣል። ከሸንጎው በተገኘው ውጤት መሠረት የሕዝብ ድርጅቱ የተባለው መረጃ ትክክለኛነት የጎደለው፣ ወይም አሳሳች፣ ወይም ምስጢራዊነትንም ሆነ ወይም ሌሎች የልጁን መብቶች የሚጋፋ ሆኖ እንዳገኘው ከወሰነ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት መረጃውን ያስተካክላል፣ አፈጻጸሙንም በጽሑፍ ለወላጆች ያሳውቃል። ከሸንጎው በተገኘው ውጤት መሠረት የሕዝብ ድርጅቱ የተባለው መረጃ ትክክለኛነት የጎደለው አይደለም፣ አሳሳችም አይደለም፣ ወይም ምስጢራዊነትንም ሆነ ሌሎች የልጁን መብቶች የሚጥስም አይደለም ብሎ ከወሰነ፣ ወላጆች በተባለው መረጃ ላይ ያላቸውን አስተያየት በማከል፣ ስለልጁ የያዙትን ተጨማሪ መረጃ የማቅረብ መብት እንዳላቸው ድርጅቱ ሊያሳውቃቸው ይገባል። በልጅዎ ሬኮርዶች ላይ የሚታከለው ማንኛውም ማብራሪያም፦

- ሬኮርዱ፣ ወይም ክርክር የተነሳበት የሬኮርዱ ክፍል የሕዝብ ድርጅቱ እጅ እስካለ ድረስ፣ የሬኮርዶቹ አካል ሆኖ በሕዝብ ድርጅቱ እጅ መቆየት አለበት፣ እንዲሁም
- የልጁ ሬኮርድ፣ ወይም ክርክር የተነሳበት የሬኮርዱ ክፍል፣ በሕዝብ ድርጅቱ አማካኝነት ለማንኛውም ሌላ ወገን ከተሰጠ፣ ማብራሪያውም ጭምር አብሮ መገለጥ አለበት።

## የመረጃ ድምሰሳ ሥርዓታዊ ክንዋኔ

የሕዝብ ድርጅቱ በ IDEA ሥር በተመለከተው መሠረት ሰብስቦት፣ አስቀምጦት፣ ተጠቅሞበት የነበረው የግለሰባዊ መለያ መረጃ ከእንግዲህ ወዲያ ለልጁ ለሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች አስፈላጊ አይድሉም ብሎ ባመነ ጊዜ፣ ይህንኑ ለወላጆች ማሳወቅ ይጠበቅበታል። መረጃውም፣ ወላጆች ሲጠይቁ የደመሰሳል። ሆኖም የተማሪው ስም፣ የስልክ ቁጥሩ፣ የትምህርት ውጤቱ፣ የተሳትፎ ሬኮርዱ፣ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ትምህርቱን የተከታተለባቸው ቀናት፣ ያጠናቀቀው የክፍል ደረጃ፣ እና ስንተኛ ዓመትን እንዳጠናቀቀ የሚያሳየው የተማሪው ቋሚ ሬኮርድ ያለምንም ጊዜ ገደብ በድርጅቱ ተይዞ ሊቆይ ይችላል።

## የልጆች መብቶች

በ FERPA ሥር በተመለተው ደንብ መሠረት፣ የልጁ የአካል ጉድለት፣ በስቴቱ ሕግ መሠረት ብቁ የሚያደርገው ካልሆነ በስተቀር፣ ልጁ 18 ዓመት ሲሞላው፣ ወላጆች በልጃቸው ላይ የነበሯቸው መብቶች ሁሉ ወደ ልጁ ይተላለፋሉ። በ IDEA ክፍል B በተመለከተው መሠረት ለወላጆች ተሰጥተው የነበሩት መብቶች ሁሉ ለአካለ መጠን ወደደረሰው ልጅ የሚተላለፉ ከሆነ፣ የትምህርት ሬኮርዶችን የሚመለከቱት መብቶችም ወደ ልጁ መዛወር አለባቸው። ሆኖም የሕዝብ ድርጅቱ በ IDEA ሥር የሚጠበቅበትን ማስታወቂያ ለወላጅና ለልጁ መስጠት አለበት። በይበልጥ የተብራራ መረጃ ለማግኘት እባክዎን "የወላጅነት መብቶችን አካለ-መጠን ለደረሱ ልጆች ማስተላለፍ" የሚለውን ይመልከቱ።

## ሥነ ምግባራዊ መረጃ

አንድ የሕዝብ ድርጅት፣ በአንድ ተማሪ ላይ የተወሰደ፣ ወይም ቀደም ሲል ተወስዶ የነበረ የሥነ-ምግባር እርምጃን የሚያሳይ መግለጫ፣ ልክ የአካል ስንክልና ለሌለባቸው ተማሪዎች በሚደረገው ተመሳሳይ የሬኮርድ መያዝና የማስተላለፍ ሁኔት፣ በልጁ ሬኮርድ ውስጥ አካትቶ ሊይዝ ይችላል፣ መግለጫውንም ያስተላልፋል። የሥነ-ምግባር እርምጃው እንዲወሰድበት የተደረገው ልጅ ባህርያት መግለጫን የተወሰዱ የሥነ-ምግባራዊ እርምጃዎችን፣ እና ማንኛውንም ለልጁ ሁለንተናዊ ደህንነት አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚገመቱ መረጃዎችና በልጁ ጉዳይ የገቡ/የተሳተፉ ሌሎች ግለሰቦችን ሊያካትት ይችላል። ልጁ ከአንድ ትምህርት ቤት ወደ ሌላ ትምህርት ሲተላለፍ፣ የሬኮርድ ዝውውሩ የልጁን ወቅታዊ IEP እና ማንኛውም ቀደም ብሎ ወይም በወቅቱ በልጁ ላይ የተወሰዱ እርምጃዎች ካሉ ማጠቃለል ይኖርበታል።

# የአካለ ስንኩል ልጆች ሥነ-ምግባር

***የሕዝብ ድርጅቱ የተወሰኑ የሥነ-ምግባር እርምጃ ልጃቸው ላይ ከወሰደ ወላጆች ትክክለኛ የሥርዓቶችና የመከላከያ ደንቦች የማግኘት መብት አላቸው። በትምህርት ዘምን ውስጥ፣ አንድ ልጅ የሰነ ሥርዓት ደንብ/ቦች በመተላለፍ ምክንያት ከ10 ቀናት በላይ እንዲወጣ ከተደረገ ተማሪው ትምህርታዊ አገልግሎቶች ሊሰጡት ይገባል።***

## ፍቺዎች

ለዚህ ክፍል አገልግሎት የሚከተሉት ፍቺዎች ይተገበራሉ፦

- የተከለከለ/ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ-ነገር ማለት ማንኛውም መድሃኒት/ዕጽ፣ ወይም በ(21 U.S.C. 812(c)) በተመለከተው የተከለከለ/ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ-ነገሮች ድንጋጌ ውስጥ በተመለከተው የአፈጻጸም መርሀ-ግብር I፣ II፣ III፣ IV ወይም V በክፍል 202(c) ሥር የተጠቀሰ ክልክል/ሕገ-ወጥ ነገር።

- ሕገ-ወጥ ንጥረ-ነገር (ድሬግ) ማለት የተከለከለ/ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ-ነገር ማለት ሲሆን፣ በሕጋዊ መንገድ ተይዞ የተገኘ፣ ወይም በጥቅም ላይ የዋለ፣ ሕጋዊ ፈቃድ ባለው የጤና ባለሙያ ቁጥጥር ሥር ወይም ሌላ በ IDEA መሠረት ስልጣን ባለው ሰው አማካኝነት ተይዞ የተገኘን፣ ወይም በጥቅም ላይ የዋለን፣ ወይም ሌላ በፌደራላዊ ሕግ ፈቃድ ሥር ያሉትን አያጠቃልልም።

- መሣሪያ የሚለው ቃል በዩናይትድ ስቴትስ ሕግ ክፍል 930 በመጀመሪያ ኑስ ክፍል (g) ርዕስ 18፣ በጽሑፍ አንቀጽ/ፓራግራፍ (2) ሥር እንደተመለከተው "አደገኛ መሣሪያ" የሚለውን የቃል ትርጉም ይይዛል።

- ብርቱ አካላዊ ጉዳት ማለት፣ እስከ ሞት በሚያደርስ አደገኛ ሁኔታ የተፈጸመ ከፍተኛ አካላዊ ጉዳትን፣ ከፍተኛ ሕመምን የሚያስከትል፣ ረዥም ጊዜ የሚቆይ ስቃይን እና በቀላሉ የማይጠፋ ጠባሳን በአካል ላይ የሚተው ከፍተኛ አካላዊ ጉዳትን፣ ወይም አካላዊ እንቅስቃሴን ለረዥም ጊዜያት የሚገታ የሰውነት አካል፣ የሰውነት ብልት፣ ወይም የአዕምሮ ጉድለትን የሚያስከትል ብርቱ አካላዊ ጉዳት ማለት ነው (18 U.S.C. 13645(h)(3))።

## የትምህርት ቤት ባልደረቦች ሥልጣን

የትምህርት ቤት ባልደረቦች፣ አንድ የትምህርት ቤቱን የሥነ ሥርዓት ደንብ የተላለፈን አካለ ስንኩል ተማሪ፣ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል በሚሠራው የትምህርት ቤቱ የሥነ ሥርዓት ፖሊሲ መሠረት፣ ልጁ የትምህርት ቤቱን የሥነ ሥርዓት ደንብ በጣሰ ቁጥር ከ10 ለማይበልጡ የትምህርት ቀናት ልጁን ከትምህርት ቤቱ ማገድ፣ የማባረሩ ሁኔታ ከወቅታዊው ምደባ ወደሚከተሉት ምደባ ለውጥ የሚያጠቃልል እንደሚሆን ካልተወሰነ በስተቀር፦
- ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት መቀበያ ቦታ፣
- ሌላ ቦታ፣ ወይም
- መታገድ።

እነዚህ ከትምህርት ቤት የመታገድ/የመባረር (በአንድ ወቅት ለ10 ወይም ከዚያ በታች ለሆኑ ቀናት) ሁኔታዎች በተደጋጋሚ ተከስተው ሲጠራቀሙ ቀይተው በትምህርት ዓመቱ የመጨረሻ ወቅት ላይ ሲደመሩ ከ10 ቀናት ብላይ ከሆኑ፣ የልጁ የ IEP ቡድን ልጁ አጠቃላዩን የትምህርት መርሀ-ግብር እና የ IEP ግቦቹን ለማሟላት ይችል ዘንድ የሚያስፈልጉትን የአገልግሎቶች መጠን ይወስናሉ።

የትምህርት ቤቱ ባልደረቦች፣ የትምህርት ቤቱን የሥነ-ሥርዓት ደንብ ለጣሰው የአካል ጉዳተኛው ተማሪ የትምህርት ምደባ ለውጥ ማድረግ የሚያስፈልግ እንደሆነ ለማየት ጉዳዩን በዝርዝር እየተመለከቱ የተለዩ ሁኔታዎች ካሉም ያጤናሉ። የምደባ ለውጥ፣ ከ10 ተከታታይ ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት ማባረርን፣ ወይም ድግግሞሽን የሚያካትት ተከታታይ መባረሮችን ያጠቃልላል። የሥነ ምግባር ጥሰት የምደባ ልውጥን የሚያስከትል ሲሆን፣ ውሳኔው የተሰጠበትን ቀን የሚያሳይ ማስታወቂያ ይሰጣል፣ ይህም የሥርዓት መከላከያዎችን ማካተት ይኖርበታል።

**<u>የገለጻ ውሳኔ</u>**

በሥነ ምግባር ጥሰት ምክንያት የተደረገን የምደባ ለውጥ ውሳኔን በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለመለወጥ፣ የሕዝብ ድርጅቱ፣ ወላጅና አስፈላጊ የሆኑ የ IEP ቡድን አባላት በጋራ በመሆን IEPን፣ ማንኛውም የአስተማሪ ትዝብትንና ግምገማዎችን፣ እና ለውሳኔው አስፈላጊነት አላቸው ተብለው በወላጆች የቀረቡትን ማንኛቸውንም ዓይነት መረጃዎች ጨምሮ መርምሮ በጥያቄ ሥር ያለው ሥነ-ምግባር፦

- በልጁ አካለ ስንኩልነት ምክንያት የመነጨ እንደሆነ ወይም ከአካለ ስንኩልናው ጋር ቀጥተኛና አሳማኝ ግንኙነት እንዳለው፣ ወይም
- በጥያቄ ሥር ያለው ሥነ-ምግባር የሕዝብ ድርጅቱ IEPውን በአግባቡ ካለመተርጎሙ በቀጥታ የመነጨ እንደሆነ።

የ IEPው ቡድን ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ከሁለት አንዳቸው ተማሪውን የሚመለከቱ እንደሆነ ከወሰኑ፣ የተጠቀሰው የሥነ-ምግባር ችግር የተማሪው የአካለ ጎደሎነት ነጸብራቅ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።

የሥነ-ምግባር ሁኔታው የልጁ አካለ ጎደሎነት ነጸብራቅ ከነበረ የ IEP ቡድኑ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፦

- ተግባራዊ የባሕርይ/የጸባይ ግምገማ ማካሄድና፣ ለተማሪው የሚረዳ የባሕርይ ማስተካከያ ጣልቃ ገብነት ዕቅድ አውጥቶ በሥራ ላይ ማዋል፣ የሕዝብ ድርጅቱ ቀደም ብሎ ይህንኑ ያላደረገ ከሆነ፣
- የባሕርይ ማስተካከያ ጣልቃ ገብነት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ባለበት ሁኔታ፣ ተማሪው ይሄው የባሕርይ ማስተካከያ ጣልቃ ገብነት ዕቅድ የነበረው ከሆነ፣ ባሕርዩን ለማረምና ለማስተካከል አስፈላጊ በሆነ መልኩ፣ ይህንኑ ነባር ዕቅዱን እንደገና መገምገምና ማሻሻል፣ እንዲሁም
- ተማሪው በዕጽ/ድረግ፣ በመሳሪያ፣ ወይም በሰው ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳትን በማድረስ ምክንያት ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የመማሪያ ቦታ እንዲዛወር በተደረገበት ሁኔታ ሳይሆን፣ ለጸባይ ማረሚያ ዕቅዱ ማሻሻያነት እንደሚረዳ በማሰብ ወላጅና የሕዝብ ድርጅቱ ለልጁ አዲስ ምደባ ቢደረግ እንደሚሻል የተስማሙ ካልሆነ ተማሪው ወደተባረረበት ትምህርት ቤቱ እንዲመለስ ማድረግ አለበት።

የሥነ-ምግባር ሁኔታው የተማሪው የአካለ ስንኩልነት ነጸብራቅ ካልሆነ ተገቢነት ያላቸው የትምህርት መርሀ-ግብሮቹ እንዲቀጥሉ ከመደረጋቸው በስተቀር፣ ይህን መሰሉን የሥነ-ምግባር ግድፈት በፈጸሙ አካለ ስንኩልነት በሌለባቸው ተማሪዎች ላይ የሚወሰዱት አግባብነት ያላቸው የሥነ-ምግባር እርምጃዎች ሁሉ በተማሪው ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

**<u>የምደባ ለውጥ</u>**

ለትምህርት ምደባው ለውጥ ምክንያት ለሆነው መባረሩ፣ አንድ ተማሪ ከ10 ቀናት በላይ ከትምህርቱ ተባሮ እንዲቆይ በተደረገ ጊዜ፣ የሥነ-ምግባሩ ሁኔታ የአካለ ስንኩልነቱ ነጸብራቅ ሆነም አልሆነ፣ ወይም ተማሪው በዕጽ/ድረግ፣ በመሳሪያ፣ ወይም በሰው ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት በማድረስ ምክንያት ወደጊዜያዊ የመሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት ቦታ (IAES) እንዲዛወር በተደረገበት ሁኔታ፣ ተማሪው፣ ምንም እንኳን በሌላ ቦታ ሆኖ ቢሆንም፣ በአጠቃላዩ ሥርዓተ-ትምህርት መሳተፉን መቀጠል እንዲችልና፣ ለተማሪው በተዘጋጀው IEP ውስጥ የተካተቱትን ግቦቹን ለማሟላት የሚያደርገውን ጥረት ለመቀጠል የሚያስችሉትን አገልግሎቶች ማግኘቱን ይቀጥላል። በተጨማሪም ተማሪው፣ እንዳስፈላጊነቱ፣ የሥነ-ምግባር ጥሰቶች በተደጋጋሚ እንዳይዘወተሩ ለማረም እንደሚረዱ ሆነው የተቀረጹ፣ ተግባራዊ የባሕርይ ግምገማና የጠባይ ማስተካከያ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችና ማሻሻያዎችን ማግኘት ይኖርበታል። የ IEP ቡድኑም ተስማሚዎቹን አገልግሎቶችና አገልግሎቶቹም የሚሰጡበትን ቦታ ይወስናል።

## መሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት መስጫ ቦታ

የትምህርት ቤት ባልደረቦች፣ የአንድ ተማሪ ሁኔታ ከታች ከተዘረዘሩት ነጥቦች ጋር ተገናዛቢነት ሲኖረው፣ የተከሰተው ሥነ-ምግባር ሁኔታው የልጁ አካለ ጎደሎነት ነጸብራቅ ስለመሆን አለመሆኑ የተደረሰ ውሳኔ ኖረም አልኖረ፣ ተማሪውን እስከ 45 የትምህርት ቀናት ድረስ ወደ መሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት መስጫ ቦታ መላክ ይችላሉ፦

- ለስቴቱ ክፍለ ግዛት ወይም ለአካባቢው የሕዝብ ድርጅት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት፣ ተማሪው፣ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ፣ በትምህርት ላይ እንዳለ፣ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ ወይም ወደ ትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ቤቱ የክብረ በዓል/ዝግጅት ቦታ ላይ መሳሪያ ይዞ ወይም ባለመሳሪያ ሆኖ ከተገኘ፣
- ለስቴቱ ክፍለ ግዛት ወይም ለአካባቢው የሕዝብ ድርጅት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት፣ ተማሪው፣ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ፣ በትምህርት ላይ እንዳለ፣ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ ወይም ወደ ትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ቤቱ የክብረ በዓል/ዝግጅት ቦታ ላይ የተከለከለ ዕጽ/ድረግ ይዞ ወይም ሲጠቀም፣ ወይም ሲሸጥ ወይም ለመሸጥ ሲያስማማ/ሲደልል ከተገኘ፣ <u>***ወይም***</u>
- ለስቴቱ ክፍለ ግዛት ወይም ለአካባቢው የሕዝብ ድርጅት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት፣ ተማሪው፣ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ፣ በትምህርት ላይ እንዳለ፣ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ ወይም ወደ ትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ቤቱ የክብረ በዓል/ዝግጅት ቦታ ላይ በሌላ ሰው ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት ካደረሰ።

## የእርማት ይግባኝ/አቤቱታ

በልጃቸው የባሕርይ ነጸብራቅ ጉዳይ ላይ የተላለፈውን ውሳኔ፣ ወይም ከሥነ-ምግባር ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የተደረገውን ምደባ ወላጆች የሚቃወሙ ከሆነ የአቤቱታ ማመልከቻቸውን ለአስተዳደራዊ ሸንጎ ቢሮ (OAH) እና ለሕዝብ ድርጅቱ በማቅረብ ጉዳዩ እንዲታይላቸው መጠየቅ ይችላሉ። የሕዝብ ድርጅቱ የልጁን ወቅታዊ ምደባ ይዞ ማቆየት ልጁ ላይ ወይም ሌሎች ላይ ጉዳት የማስከተሉ ዕድል ከፍተኛ ነው ብሎ ካመነ፣ የሕዝብ ድርጅቱ ጉዳዩ እንዲታይለት የአቤቱታ ማመልከቻ OAH እና ለወላጆች ሊያስገባ ይችላል።

የአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ)፣ እዚህ ሰነድ ውስጥ "አለመግባባቶችን ስለመፍታት" በሚለው ክፍል ውስጥ በተዘገው ሥርዓት መሠረት፣ የፍትህ ሂደት ያካሂዳል። ጉዳዩ ለሸንጎው ቀርቦ እንዲሰማ ከተጠየቀበት ቀን አንስቶ በ20 የትምህርት ቀናት ውስጥ ለቀርብ የሚችል ሲሆን፣ ጉዳዩ በተሰማ በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥም ከአንድ ውጤት ላይ ይደረሳል።

በእርማት ይግባኝ ላይ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ፣ ALJ፦

- ልጁ ቀደም ብሎ ወደተባረረበት ትምህርት ቤት እንዲመለስ ሊያደርግ ይችላል፣ ወይም

- ልጁ አሁን ባለበት ምደባው እንዳለ መቆየቱ በተማሪው በራሱ ላይም ሆነ በሌሎች ተማሪዎች ላይ ተጨባጭ ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል ብሎ ከወሰነ፣ ይህ ተማሪ ከ45 ለማይበልጡ የትምህርት ቀናት ወደተስማሚ የመሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት መስጫ ቦታ እንዲቀየር ተዕዛዝ ይሰጣል።

በወላጅ ወይም በሕዝብ ድርጅት አቤቱታ በቀረበ ጊዜ፣ የALJውን ውሳኔ በመጠባበቅ፣ ወይም የተፈቀደው የጊዜ ገደብ (ከ45 የትምህርት ቀናት የማይበልጥ) እስከሚያበቃ፣ ቀድሞ የሚሆነው እስከሚሆን ድረስ፣ ተማሪው በመሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት መስጫ ቦታ ላይ ይቆያል፣ ወላጁቹ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ በተቃራኒው ካልተስማሙ በስተቀር።

## ልጁ ገና ብቁ ሆኖ ካልተገኘ

ለልዩ ትምህርት ብቁ መሆናቸው ገና ሳይወሰን በፊት ማንኛውንም ደንብ ወይም ሥነ-ምግባር የጣሱ ተማሪዎችን በሚመለከት፣ ይህ የባሕርይ ግድፈት ከመከሰቱ በፊት፣ ተማሪው አካለ ስንኩልነት እንደነበረበት ይሕዝብ ድርጅቱ የሚያውቅ ከሆነ፣ የተፈቀደው መከላከያ ይገባናል ብለው ተማሪዎቹ ሊጠይቁ ይችላሉ። የሕዝብ ድርጅቱ ያውቃል የሚባለው፣ የሥነ-ምግባር እርምጃውን ለመውሰድ ምክንያት የሆነው የባሕርይ ግድፈት ከመከሰቱ በፊት፦

- የተባለው ተማሪ፣ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉት፣ ወላጆች ስጋታቸውን ለወረዳው (ለዲስትሪክቱ) የቁጥጥር/ክትትል ወይም አስተዳደራዊ አባል፣ ወይም ለልጁ አስተማሪ፣ በጽሑፍ ገልጸው ከሆነ፣
- ወላጆቹ የግምገማ ጥያቄ አቅርበው እንደሆነ፣ ወይም
- የተማሪው አስተማሪ፣ ወይም ሌላ የትምህርት ቤቱ ባልደረባ፣ በልጁ ላይ የተስተዋሉ በግልጽ የሚታወቁ ተደጋጋሚ የሥነ-ምግባር/የባሕርይ ሁኔታዎችን አስመልክቶ፣ ያደረባቸውን ስጋት በቀጥታ ለልዩ ትምህርት ሥራ መሪው፣ ወይም ለሌላ የሕዝብ ድርጅት የቁጥጥር/ክትትል ባልደረባ ገልጸው ከሆነ።

የሕዝብ ድርጅቱ አላወቀም የሚባለው፦

- ወላጆች የሕዝብ ድርጅቱ ልጃቸውን እንዲገመግም ካልፈቀዱ፣
- ወላጆች የሕዝብ ድርጅቱ ለልጃቸው የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች እንዲሰጥ ካልፈቀዱ፣ ወይም
- ልጁ ተገምግሞ በ IDEA ፍቺ መሠረት አካለ ስንኩልነት ያለበት ልጅ እንዳልሆነ ከተወሰነ።

የሕዝብ ድርጅቱ፣ የሥነ-ምግባር እርምጃውን ከመውሰዱ ቀደም ብሎ ስለ ልጁ አካለ ጎደሎነት ሁኔታ የማያውቅ ከሆነ፣ ልጁ አንድ በተመሳሳይ የሥነ-ምግባር ጉድለት ላይ የተገኘ የአካል ጉድለት የሌለበት ተማሪ ከሚወሰድበት ተመሳሳይ የሥነ-ምግባር እርምጃን የመቀበል ዕጣ ሥር ይወድቃል።

ለተማሪው ግምገማ እንዲደረግለት ጥያቄው የቀረበው፣ ተማሪው በወቅቱ በሥነ-ምግባር እርምጃ ሥር ባለበት ወቅት ከሆነ፣ ግምገማው በአፋጣኝ መደረግ ይኖርበታል። የውሳኔዎቹን ወጤቶች በመጠባበቅ ልይ ሳለም፣ ልጁ በትምህርት ቤቱ ባለሥልጣናት በተወሰነው የትምህርት ምደባ ላይ ይቆያል። በሕዝብ ድርጅቱ ግምገማና በወላጆች በቀረበው መረጃ ላይ በመመሥረት፣ ልጁ አካለ ስንኩልነት አለበት ተብሎ ከተወሰነ፣ የሕዝብ ድርጅቱ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ያቀርቡለታል፣ ከዚያም ሥነ-ምግባርን/ሥነ-ሥርዓትን የሚመለከቱ ሁሉም የሥርዓት መከላከያዎች ይከተላሉ።

__ወደ ሕግ አስከባሪና የዳኝነት ባለሥልጣናት መተላለፍና የሚወሰድ እርምጃ__

IDEA የሕዝብ ድርጅቶች አንድን ወንጀል፣ አግባብነት ላላቸው ባለሥልጣናትና ለሕግ አስከባሪ መዝገብ/ሪፖርት ከማድረግ አይከለክልም። የዳኝነት ባለሥልጣናትም በአንድ አካለ ስንኩል ልጅ ለተፈጸሙ ወንጀሎች የፌዴራላዊና ክፈለ ግዛታዊ ሕግጋትን በተግባር በማስፈጸም ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይችላሉ። ማንኛውም የወንጀል ዘገባን የሚያቀርብ ድርጅት፣ በ COMAR 13A.08.02 እስከተፈቀደው ድረስ በመሄድ፣ የወላጅ ፈቃድ ተጨምሮበት፣ ወይም በፖሊሲው ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት የወላጅ ፈቃድ የማይጠየቅባቸውንም በማካተት፣ የልዩ ትምህርትና ሥነ-ምግባራዊ ሬኮርዶችን ቅጂዎች አግባብነት ላላቸው ባለሥልጣናት ያቀርባል።

## ወላጆች በግለኝነት ልጆቻቸውን የግል ትምህርት ቤት ውስጥ በሕዝብ ወጪ ስለማስገባት

***IDEA፣ አንድ የሕዝብ ድርጅት አንድ ልጅ የነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት (FAPE)እንዲያገኝ አማራጭ ቢሰጠውም ወላጆቹ በፈቃደኝነት ልጃቸውን የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ማስገባት ከመረጡ የሕዝብ ድርጅቱ፣ በግል ትምህርት ቤት ውስጥ ያለን የአንድ አካለ ስንኩል ልጅን የትምህርት ወጪ፣ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ጨምሮ እንዲከፍል አያደርገውም።***

አንድ የሕዝብ ድርጅት፣ ለተባለው ልጅ የሚመጥን FAPE ዝግጁ አድርጎ ባለበት ወቅት፣ ወላጆች ግን በራሳቸው ምርጫ ልጃቸውን በግል ትምህርት ቤት፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ አገልግሎት ካለበት ቦታ ማስገባት ከፈለጉ፣ ለልጁ የሚጠየቀውን የልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ወጪ፣ የ FAPEውን ዝግጁ አድርጎ የነበረው ቀዳሚው የሕዝብ ድርጅት እንዲከፍል IDEAው አያዝበትም። ሆኖም በፌዴራል ደንቦች መሠረት የሕዝብ ድርጅቱ ልጁን ወላጆቻቸው የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ከከቷቸው ልጆች መሃል አንድ አድርጎ ማስገባት አለበት። የ FAPEን ዝግጁነትና የገንዘብ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ፣ በወላጆችና በሕዝብ ድርጅቱ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣ በ IDEA ሥር በተመለከተው መሠረት፣ ከፍርድ ሸንጎ/ችሎት ፊት ቀርበው የዳኝነት ፍርዳቸውን ማግኘት ይኖርባቸዋል። ለበለጠ ዝርዝር መረጃ፣ "አለመግባባቶችን ስለመፍታት" የሚለውን ይመልከቱ።

ቀደም ሲል በአንድ የሕዝብ ድርጅት ሥልጣን ሥር፣ ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ሲያገኑ የነበሩ የአንድ አካለ ጎደሎ ተማሪ ወላጆች፣ ከሕዝብ ድርጅቱ ፈቃድ ሳያገኙ፣ ወይም በሕዝብ ድርጅቱ ባልተፈጸመ ዝውውር፣ ልጃቸውን በመዋለ-ሕጻናት ትምህርት ቤት፣ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲገባ ቢያደርጉና፣ ልጁ ወደ አዲሱ የሚማርበት ቦታ ከመዛወሩ በፊት የሕዝብ ድርጅቱ ለልጁ የሚስማማ FAPE ዝግጁ ያላደረገ እንደነበረ በ ALJ ወይም በፍርድ ቤቱ ከተረጋገጠ፣ አሁን በግል የተደረገለት የትምህርት መቀበያ ቦታም ለልጁ ተስማሚ እንደሆነ ከታመነበት፣ ALJው ወይም ፍርድ ቤቱ ወላጆች ለልጃቸው የአዲሱ ምደባው ያወጡትን ወጪ ድርጅቱ እንዲከፍል ሊያዘው ይችላል። ምንም እንኳን የሀገሪቱን የትምህርት ጥራት መለኪያዎች መሠረት በማድረግ በሕዝብ ድርጅቶች የሚቀርቡትን የትምህርት ጥራት መለኪያዎች የሚያሟሉ ባይሆኑም፣ በወላጆች የሚደረጉ የትምህርት ቤት ምደባዎች በ ALJው ዘንድ የስማሚ እንደሆኑ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ።

__በወጪዎች ማካካሻ ላይ ገደብ__

የወጪ ማካካሻ በ ALJ ወይም በፍርድ ቤት ሊቀነስ ወይም ሊከለከል የሚችለው፦

- ልጁ ከመንግሥት ትምህርት ቤቱ ከመታገዱ ቀደም ብሎ በተደረገ ወላጆችም በተሳተፉበት የቅርብ ጊዜ የ IEP ቡድን ስብሰባ ላይ፣ ወላጆች እርምጃውን ለመውሰድ ያሳሰባቸውን/ያነሳሳቸውን ጉዳዩና ልጁን በሕዝብ ወጪ በሚንቀሳቀስ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ለማስገባት የፈለጉበትን ምክንያት ጭምር በመዘርዘር፣ የሕዝብ ድርጅቱ ለልጁ የሚስማማ FAPE ለማሰናዳት ያቀረበውን ሐሳብ አለመቀበላቸውን ለ IEP ቡድኑ ያላሳወቁ ከሆነ፣ ወይም

- ልጁ ከመንግሥት ትምህርት ቤት እንዲወጣ ከመደረጉ በፊት አሥር (10) የሥራ ቀናት (በዓል ሆነው የዋሉ የሥራ ቀናትንም ጀምሮ) ቀደም ብለው ወላጆች የልጃቸውን ሕዝባዊ ምደባ አስመልክቶ ያሳሰባቸውን ጉዳይ በማካተት ልጁን ከሕዝብ ትምህርት ቤት እንድዲለቅ ለማድረግ ያነሳሳቸውን ሓሳብ በጽሑብ ለሕዝብ ድርጅቱ ያላሳወቁ ከሆነ፣ ወይም

- ወላጆች ልጃቸውን ከመንግሥት ትምህርት ቤት ከማስወጣታቸው ቀደም ብሎ፣ የሕዝብ ድርጅቱ አንድን ልጅ ለመገምገም ሲ.ታሰብ ለወላጆች የሚሰጠውን የቀዳሚ ማስታወቂያ መርህ በመከተል (ተገቢና የመጣጣኝ ነው ተብሎ የቀረበውን የግምገማ ዓላማ የሚያካትት መግለጫን በማከል) የሕዝብ ድርጅቱ ለወላጆች የጽሑፍ ማስታወቂያውን በመስጠት አሳውቋቸው ከሆነ፣ ወይም

- ወላጆች የወሰዱት እርምጃ አሳማኝ ምክንያት የሌለው መሆኑ በዳኞች ምርመራ ከተረጋገጠ።

ከላይ የተዘረዘሩት የማስታወቂያ አስፈላጊነቶች እንዳሉ ሆነው፣ የወጪ ማካካሻ (ተመላሽ)፦

- ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ምክንያት ወላጆች የተባለውን ማስታወቂያ በወቅቱ ባለመስጠታቸው ብቻ ሊቀነስ ወይም ሊከለከል አይችልም፦
  - ወላጆች ማስታወቂያውን እንዳይሰጡ ትምህርት ቤቱ ከልክሏቸው ከሆነ፣
  - ከላይ በተገለጡት የIDEA የማስታወቂያ አስፈላጊነቶች መሠረት ወላጆች ምንም ምስታወቂያ ያልደረሳቸው ከሆነ፣
  - ከላይ የተጠቀሰው ማስታወቂያ ተከብሮ በተግባር ቢ.ተረጎም፣ በልጁ ላይ ሊያስከትለው የሚችል የአካላዊ ጉዳት አዝማሚያ ተሰተውሎ ከሆነ፣ እንደዚሁም

- ምናልባትም፣ የሚከተሉትን ሁኔታዎች በማጤን ፍርድ ቤት ወይም ALJ በሚሰጠው አመዛዛኝ ውሳኔ መሠረት፣ ወላጆች የተባለውን ማስታወቂያ ባለማቅረባቸው የወጪ ማካካሻው ሊቀነስ ወይም ሊከለከል አይችልም ከተባለ፦
  - ወላጆች ያልተማሩ ከሆኑ እና በእንግሊዝኛ መጻፍ የማይችሉ ከሆነ፣ ወይም
  - ከላይ የተጠቀሰው ማስታወቂያ ተከብሮ በተግባር ቢ.ተረጎም፣ በልጁ ላይ ሊያስከትለው የሚችል የመንፈሳዊ ጉዳት አዝማሚያ ተሰተውሎ ከሆነ።

## የወላጅነት መብትን አካለ-መጠን ለደረሱ ልጆች ማስተላለፍ

***በሜሪላንድ ውስጥ፣ በአንዳንድ በልዩ ሁኔታዎች ጊዜ ካልሆነ በስተቀር፣ ልጆች ለአካለ-መጠን በደረሱ ጊዜ የወላጅ መብቶች ወደ አካለስንኩል ልጆች አይተላለፉም።***

በሜሪላንድ ሕግ ሥር እንደተመለከተው፣ በIDEA ሥር ለወላጆች የተሰጡት ሁሉም መብቶች፣ በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ አካለስንኩልናው ወዳለበት ልጃቸው ይተላለፋሉ። ተማሪው የአእምሮ ብቃት እንደሚጎድለው በስቴቱ ሕግ መሠረት ካልተረጋገጠበት <u>እና</u> የሚከተሉትን መጠይቆች የሚያረጋግጡ ሰነዶች ካሉ፣ ተማሪው 18 ዓመት ሲ.ሞላው ነው፣ ይህ የመብት መተላለፍ የሚፈጸመው። ተጠናቅረው የተያዙ ሰነዶች የሚባሉትም፦

- ወላጆች ያልተገኙ ወይም ያልታወቁ እንደሆነና፣ ልጁም የወላጅ ምትክ ከሚመደብለት ይልቅ የወላጅነት መብቶች ወደሱ እንዲተላለፉለት የጠየቀበት ሰነድ ካለ፣

- ቀደም ባሉት ዓመታት፣ የሕዝብ ድርጅቱ ወላጆች በልጁ የልዩ ትምህርት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ እንዲሳተፉ ወላጆችን በተደጋጋሚ ቢ.ጠይቅም፣ ወላጆች ግን ያልተሳተፉ መሆናቸውን የሚያሳይ ሰነድ ካለ፣

- ወላጆች በልዩ ትምህርት የውሳኔ አሰጣጡ ሂደት ላይ በመሳተፍ ዝግጁ አለመሆናቸውን ያረጋገጡበት ሰነድ ካለ፣

- ወላጆች በሕመም ምክንያት ለረጅም ጊዜ በሆስፒታል በመተኛታቸው፣ በማገገሚያ ሁኔታ ውስጥ በመሆናቸው፣ ወይም በብርቱ ሕመም/የጤና መታወክ ምክንያት፣ ከወላጆቹ አንዱ ወይም ሁለቱም የአቅም/የሰውነት መዳከም ውስጥ ያሉ በመሆኑ፣ ይህ መብት ከእንግዲህ ለልጁ እንዲተላለፍ በማለት ስምምነታችውን የሰጡበት ሰነድ ካለ፣

- ወላጆች ከቁጥጥራቸው ውጪ የሆነ ልዩ ችግር አጋጥሟቸው በልዩ ትምህርት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ለመሳተፍ ባለመቻላቸው፣ በዚህም የተነሳ የወላጅነት መብታቸው ወደ ልጃቸው እንዲተላለፍላቸው ስምምነታቸውን የሰጡ ለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ሰነድ ካለ፣ <u>ወይም</u>

- ልጁ ከወላጆቹ ቤት ውጪ የሚኖር ከሆነና፣ በሌላ የሕዝብ ድርጅት እንክብካቤ ሥር እንዳልሆነ የሚያረጋግጡ ሰነዶች ካሉ፣ የሚሉት ናቸው።

ልጃቸው አብሯቸው የሚኖር የሆኑ የአካለስንኩል ተማሪ ወላጆች፣ ልጁ 18 ዓመት ሲሞላው የወላጅነት መብታቸውን ወደ ልጃቸው ለማስተላለፍ ባይስማሙና ልጁም የአእምሮ ብቃት ጉድለት እንዳለበት በስቴቱ ሕግ መሠረት ካልተረጋገጠበት በስተቀር፣ ከሁለቱ ወገኖች አንዳቸው ጉዳዩ በችሎት እንዲታይላቸው በማለት ማመልከቻውን ሊያስገቡ ይችላሉ።

አንድ አካለስንኩል ተማሪ የፌዴራላዊና ስቴት ሕግጋት በሚደነግጉት መሠረት በወላጅ ምትክ ተወክሎ ከሆነ፣ የሕዝብ ድርጅቱም በፌዴራላዊና ስቴት ሕግጋት ሥር በታዘዘው መሠረት፣ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለተማሪውና ለወላጅ ተተኪው ግለሰብ ነው የሚሰጠው። ሌሎች በ IDEA ሥር ለተተኪው የወላጅ ምትክ ሁሉም መብቶች፣ ተማሪው በክፍለ ግዛቱ ሕግ መሠረት የአእምሮ ብቃት እንደሚጎድለው ካልተረጋገጠበት በስተቀር <u>እና</u> ተማሪውም መብቶቹ ወደ እርሱ (ተማሪው) እንዲተላለፉለት ከጠየቀ፣ መብቶቹ ወደጠያቂው ተማሪ ይተላለፋሉ።

## አለመግባባቶችን ስለመፍታት

***የሚከተሉት ሥርዓታዊ አሠራሮች የአንድ ልጅን ልዩ ትምህርት መርሀ-ግብርና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የተመለከቱ አለመግባባቶችን ስለመፍታት ለወላጆችና ለሕዝብ ድርጅቶች ይገልጻሉ።  አማራጮቹ ግልግልን፣ የስቴት አቢቱታንና የፍትህ ሂደት አቤቱታን ያካትታሉ።***

### <u>ግልግል</u>

በአካለስንኩል ልጅ ወላጆችና በልጁ ትምህርት ኃላፊ በሆነው የሕዝብ ድርጅቱ መካከል አለመግባባቶችን ለመፍታት የግልግል ሂደትን መጠቀም ይቻላል።

አንድ ስለግልግል ስልቶች/ቴክኒኮች ተገቢውን ሥልጠና የወሰደ የአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ (OAH) ሠራተኛ የሆነ ሰው የግልግሉን ሂደት ይመራል።

- ግልግል ለወላጅ ወይም ለልጁ ትምህርት ኃላፊ ለሆነው የሕዝብ ድርጅት ያለ ምንም ወጪ ይካሄዳል፣ ግልግሉን ለማበረታታት ሊባል ከወላጆች ጋር ለተደረገ ግንኙነት የወጣውን ወጪም ጨምሮ።
- የግልግል ጥያቄ የሚቀርበው ለልጁ ትምህርት ኃላፊ ለሆነው የሕዝብ ድርጅትና ለOAH ነው።  ወላጆች የግልግል ጥያቄ ሲሞሉ እርዳታ እንዲሆናቸው፣ ፎርም ከሕዝብ ድርጅቱ ወይም ከ MSDE ዌብሳይት በ www.marylandpublicschools.org አድራሻ ማግኘት ይቻላል። በይበልጥ እርዳታ ለማግኘት የሕዝብ ድርጅቱን የልዩ ትምህርት ቢሮ ይገናኙ ወይም የ MSDEን ልዩ ትምህርት/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ክፍልን በስልክ ቁጥር (410) 767-7770 ይገናኙ።
- በግልግሉ ወቅት ወላጆች ወይም የሕዝብ ድርጅቱ አማካሪዎች አብረዋቸው ሊኖሩና ሊያማክሯቸው ይችላሉ።
- የግልግል ጥያቄው በቀረበ በ20 ቀናት ውስጥ ለወላጆችና ለሕዝብ ድርጅቱ አመቺ በሆነ ቦታ እንዲካሄድ ይመቻቻል።
- የግልግል ስብሰባዎች ዝግ ሂደቶች ናቸው።  በግልግሉ ወቅት የሚካሄዱ ውይይቶች፣ በምስጢር የሚጠበቁ ሲሆን፣ በቀጣይ ሂደት ለሚታይ ማንኛውም የፍትህ ሂደት ወይም የማህበራዊ እርምጃ በማስረጃነት ሊቀርቡ አይችሉም።  ግልግሉ ከመጀመሩ በፊት ወላጆች ወይም የሕዝብ ድርጅቱ፣ ጉዳዩን በምስጢር መጠበቅ እንደሚገባቸው የሚያረጋግጥ መተማመኛ መፈረም ይኖርባቸዋል።
- በግልግሉ ውስጥ በነበሩ ወገኖች መካከል የተደረሰበት ስምምነት በጽሑፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ይኸውም ይህንን ዓይነት ጉዳይ የመስማት ሥልጣን ባለው የስቴት ፍርድ ቤት ውስጥ ወይም ፌዴራል የአውራጃ ፍርድ ቤት ውስጥ በሕግ መከበር የሚችል ይሆናል።
- አንድ የሕዝብ ድርጅት ግልግሉን ተጠቅሞ የአንድን ወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታ መብት መከልከል ወይም ማጓተት አይችልም።

### <u>ግልግልን ለማበረታታት መገናኘት</u>

የግልግል ሂድትን ላለመጠቀም የመረጡን ወላጆች፣ አንድ የሕዝብ ድርጅት ለወላጆቹ በሚመች ሰዓትና ቦታ ተገናኝቷቸው የግልግልን ጥቅም ለማስረዳትና ወላጆች የግልግልን ሂድት እንዲጠቀሙ ለማበረታታት መሞከር ይችላል።

## <u>በስቴት አቤቱታና በፍትህ ሂደት አቤቱታ መካከል ያለው ልዩነት</u>

***ከግልግል በተጨማሪ፣ ወላጆች ከሕዝብ ድርጅቱ ጋር የገጠማቸውን አለመግባባት ለመፍታት የስቴት አቤቱታ ሂደት ወይም የፍትህ አቤቱታ ሂደት የመጠቀም መብት አላቸው። እነዚህ አማራጮች ልዩ ሕጎችና ሥርዓተ ሂደቶች አሏቸው።***

የIDEA መተዳደሪያ ደንቦች ለስቴት አቤቱታዎችና ለፍትህ ሂደት አቤቱታዎች ልዩ ልዩ የሥርዓት ሂደቶች አሉት። ከዚህ በታች እንደተብራራው፣ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት አንድ የሕዝብ ድርጅት የ IDEAን ደንብ ጣሰ በሚልበት ጊዜ የስቴት አቤቱታ ማመልከቻ ማስገባት ይችላል። የልጁ መታወቂያን፣ ግምገማን ወይም አካለስንኩል የሆነን ልጅ ምደባን፣ ወይም የነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርትን (FAPE) በተመለከተ ሁሉ ወላጅ ወይም የሕዝብ ድርጅት ብቻ ናቸው የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማመልከቻ ማስገባት የሚችሉት።

የMSDE ባልደረባዎች ባብዛኛው የስቴት አቤቱታን መፍታት ያለባቸው፣ የጊዜ ገደቡ በተገቢ መንገድ ካልተራዘመ በስተቀር፣ በ60 ቀን የጊዜ ገደብ ውስጥ ነው። ወላጅ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ የጊዜ መራዘም ጥያቄ ካላቀረቡ በስተቀር፣ ALJው የፍትህ ሂደት አቤቱታውን በሸንጎ አዳምጦ (በአለመግባባት መፍቻ ስብሰባ ወይም በግልግል ካልተፈታ ማለት ነው) የችግር መፍቻ ጊዜው ባለቀ በ45 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽሑፍ ውሳኔ መስጠት አለበት።

የእነዚህን አማራጮች አጭር መግለጫና ማወዳደሪያ ለማየት እዚህ ሰነድ ውስጥ የቀረበውን ተያያዥ ሰነድ ይዩ።

## <u>የስቴት አቤቱታ</u>

***ግለሰቦችና ድርጅቶች ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ጋር (MSDE) የስቴት አቤቱታ የማስገባት መብት አላቸው። ስቴቱ ምርመራ ማካሄድ እንዲችል ዘንድ፣ በጽሑፍ የቀረበው አቤቱታ የIDEA መተዳደሪያ ደንቦችን በትክክል መከተል አለበት።***

አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት አንድ የሕዝብ ድርጅት የልዩ ትምህርትን ደንብ በተመለከተ የፌዴራል ወይም የስቴት ሕግ ጥሷል ብሎ ካመነ ወይም ይኸው የሕዝብ ድርጅት የፍትህ ሂደት ውሳኔ በሥራ ላይ አላወለም ብሎ ካመነ፣ የስቴት አቤቱታ ማስገባት ይቻላል።፡ የአቤቱታው ማመልከቻ MSDE ጋር መግባት ያለበት ሲሆን መላክ ያለበትም ለሚከተለው ነው፦ Assistant State Superintendent, Division of Special Education/Early Intervention Services, MSDE, 200 West Baltimore Street, Baltimore, Maryland 21201. ከ MSDE ጋር የስቴት አቤቱታ የሚያስገባው ግለሰብ ወይም ድርጅት የአቤቱታውን ግልባጭ ለሕዝብ ድርጅቱ በአንድ ጊዜ መላክ አለበት። የአቤቱታ ማመልከቻውን ለማስገባት እንዲረዱ በዝርዝር የተጻፉ ሥርዓተ ሂደቶችና ፎርም የ MSDE ዌብሳይት ላይ በ www.marylandpublicschools.org አድራሻ በመሄድ ይገኛሉ፣ ወይም የክፍሉ የአቤቱታ ምርመራና የፍትህ ሂደት ቅርንጫፍ ጋር በስልክ ቁጥር 410-767-7770 በመደወል።

የስቴት አቤቱታው ማካተት ያለበት፦

- የሕዝብ ድርጅቱ የፌዴራል ወይም የስቴት ሕግ ወይም ደንብ እንደጣሰ የሚናገር መግለጫ፣
- ይህ መግለጫ የተመሠረቱበትን ተጨባጭ ነገሮች፣
- የስቴት አቤቱታውን የሚያስገባውን ግለሰብ/ድርጅት ፊርማና የመገናኛ መንገድ፣ እና
- የስቴት አቤቱታው ከአንድ የተወሰነ ልጅ ጋር የተያያዘ የሕግ መጣስ ከሆነ፦
  - የልጁ ስም እና የመኖሪያ አድራሻ፣
  - ልጁ የሚማርበትን የትምህርት ቤት ስም፣
  - ልጁ ወይም ወጣቱ ቤት አልባ ከሆነ፣ ሊገኝ የሚቻለውን መገናኛ ዘዴ እና ልጁ የሚማርበትን የትምህርት ቤት ስም፣
  - የልጁ ችግር ዓይነት ማብራሪያ፣ ከችግሩ ጋር የተያያዙ ተጨባጭ ነገሮችን ጨምሮ፣
  - ለችግሩ መፍትሔ ተብሎ የቀረበውን፣ የስቴቱ አቤቱታ በገባበት ጊዜ አመልካቹ እስከሚያውቀውና ማግኘት እስከሚችለው ድረስ።

አንድ የስቴት አቤቱታ ተከስቷል የሚለው የሕግ መጣስ፣ አቤቱታው ስቴቱ ጋር ከመድረሱ ቀን እስከ አንድ ዓመት ቀድሞ ባለው ጊዜ ውስጥ የሆነ መሆን አለበት። MSDE ውሳኔውን የስቴት አቤቱታው በደረሳቸው በ60 ቀን ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፣ የ60 ቀን የጊዜ ገደቡን ማራዘም የሚችሉት የሚከተሉት ከሆኑ ነው፦

- አሁን የሚገኘውን አቤቱታ በተመለከተ ልዩ አጋጣሚዎች ካሉ፣ ወይም

- ጉዳዩ ውስጥ ያሉበት ወላጅና የሕዝብ ድርጅት አለመግባባቱን ለመፍታት ግልግልን ወይም ሌሎች መንገዶች ለመሞከር ፈልገው የጊዜ ገደቡን በፈቃደኝነት ለማራዘም ከተስማሙ።

ቢያንስ ቢያንስ MSDE የሚከተሉትን ያደርጋል፦

- አስፈላጊ ነው ተብሎ ከተወሰነ፣ ቦታው ላይ የሚደረግ የግል ምርመራ ማካሄድ፣

- አቤቱታ አቅራቢው፣ የስቴት አቤቱታ ውስጥ ስለ ክሶቹ ተጨማሪ መረጃ በቃል ወይም በጽሑፍ መስጠት እንዲችል ዕድል መስጠት፤

- ከጉዳዩ ጋር የሚያያዘውን መረጃ ሁሉ ገምግሞ የሕዝብ ድርጅቱ የፌዴራልና የስቴት ሕጎችን ስለመጣሱ የግል ውሳኔ ማድረግ፣ እና

- ለአቤቱታ አቅራቢውና ለሕዝብ ድርጅቱ አቤቱታ ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ክሶች የሚመለከት ውሳኔና የተገኙትን ተጨባጭ ነገሮችና ግምገማዎች በጽሑፍ መስጠት።

ውሳኔው የመጨረሻ ውሳኔ ይተሰጠበትን ምክንያቶችና የመጨረሻ ውሳኔውን በሥራ ላይ ለማዋል መከተል ያለባቸውን ሥርዓታዊ መንገዶች ያጠቃልላል - አስፈላጊ ከሆነም የቴክኒክ እርዳታ ድርጊቶችን፣ ድርድሮችና ሕግ የማክበሪያ የማረሚያ ድርጊቶችን ያካትታል። MSDE አንድ የሕዝብ ድርጅት ተገቢ አገልግሎችን አላሟላም ብሎ ከወሰነ በጽሑፍ የሚቀርበው የመጨረሻ ውሳኔ የሕዝብ ድርጅቱ የከለከለውን ለልጁ ተገቢ የሆኑትን አገልግሎች እንዴት ማረም እንደሚችል፣ እንዲሁም ወደፊት ለአካለስንኩል ልጆቸች በሙሉ የሚሰጡ ተገቢ አገልግሎቶችን ጨምሮ ይናገራል።

<u>የስቴት አቤቱታን ስለመፍታት</u>

ግልግል ወይም ሌሎች ኦፊሲዬላዊ ያልሆኑ የአለመግባባት መፍቻ መንገዶች ሊኖሩ ይችላሉ፣ እነሱን መጠቀምም የሚበረታታ ነው። ሁለቱ ወገኖች አቤቱታውን ከፈቱት፣ MSDE በፌዴራል ደንቦች መሠረት ምርመራ ማካሄድ የለበትም።

<u>የፍትህ ሂደት አካል የሆነ የስቴት አቤቱታን ስለመፍታት</u>

If MSDE የፍትህ ሂደት አካል የሆነ የስቴት አቤቱታ ቢደርሰው፣ ወይም አንድ የስቴት አቤቱታ በርካታ ችግሮች የያዘ ሆኖ ከእነዚህ አንዱ ወይም ብዙው የችሎት አካል ከሆኑ፣ MSDE የስቴት አቤቱታውን ማንኛውም የፍትህ ሂደት ውስጥ ያለውን ክፍል የፍትህ ሂደቱ እስከሚጠቃለል ድረስ ወደ ጎን ማስቀመጥ አለበት። ሆኖም የስቴት አቤቱታ ውስጥ ያለ ማንኛውም የፍትህ ሂደቱ ክፍል ያልሆነ ጉዳይ የጊዜ ገደቡና ከላይ የተጠቀሱትን የሥርዓት ሂደቶች ተከትሎ መፈታት አለበት። ከዚህ በፊት በፍትህ ሂደት ውሳኔ የተሰጠው ጉዳይ በስቴት አቤቱታ ውስጥ ቢነሳ፣ እና ይህ ጉዳይ እነዚሁኑ ወገኖች የሚመለከት ከሆነ፣ የችሎት ፍርዱ የሚያስገድድ ቃል ሲሆን፣ MSDEም አቤቱታ አቅራቢውን ይህንኑ መረጃ ይነግረዋል።

## <u>የፍትህ ሂደት አቤቱታ</u>

***የልጁ መታወቂያን፣ ግምገማን ወይም አካለስንኩል የሆነን ልጅ ምደባን፣ ወይም የነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርትን (FAPE) በተመለከተ ሁሉ ወላጅ ወይም የሕዝብ ድርጅት የፍትህ ሂደት ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ።***

የፍትህ ሂደት አቤቱታው የተመሠረተበት ተብዬ የሕግ መጣስ ድርጊት የተከሰተው ወላጁ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ ካወቀ ወይም ማወቅ ከነበረበት እስከ ሁለት ዓመት በፊት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት።

የሕዝብ ድርጅቱ አውቆ በፍትህ ሂደት አቤቱታ ውስጥ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ሳይፈቱ ተፈትተዋል ካለ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ በ IDEA ሥር ለወላጅ መስጠት የነበረበትን መረጃ ሳይሰጥ በመቅረቱ ምክንያት ወላጅ በጊዜ ገደብ ውስጥ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማመልከቻ ማስገባት ካልቻለ ይህ የጊዜ ገደብ በሥራ ላይ አይውልም።

የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማመልከቻ ለማስገባት፣ ወላጅ ወይም የሕዝብ ድርጅት (ወይም የወላጅ ጠበቃ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ ጠበቃ) ለሌላው ወገንና ለ OAH የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማቅረብ አለበት። አቤቱታው ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሁሉ የያዘና በምስጢር የሚጠበቅ መሆን አለበት።

ወላጆች የፍትህ ሂደት አቤቱታ ሲያስገቡ ለመርዳት የግልግልና የፍትህ ሂደት አቤቱታ ጥያቄ ማቅረቢያ ፎርም ላጃቸው ትምህርት ቤት ከሚሄድበት የሕዝብ ድርጅት ወይም ከ MSDE ዌብሳይት በ www.marylandpublicschools.org አድራሻ ማግኘት ይችላሉ። በይበልጥ እርዳታ ለማግኘት የሕዝብ ድርጅቱን የልዩ ትምህርት ቢሮ ወይም የMSDEን የልዩ ትምህርትና የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ክፍልን በስልክ ቁጥር (410) 767-7770

**የፍትህ ሂደቱ አቤቱታ ይዞታ**

የፍትህ ሂደት አቤቱታው የሚከተሉትን መያዝ አለበት፦

- የልጁን ስም፣
- የልጁን የመኖሪያ ቤት አድራሻ (ወይም ቤት አልባ ልጅ ከሆነ፣ የተገኘውን የመገናኛ መንገድ መረጃ)፣
- ልጁ የሚማርበትን የትምህርት ቤት ስም፤
- የልጁ ትምህርት ኃላፊ የሆነውን የሕዝብ ድርጅት ስም (ለምሳሌ የአካባቢው የትምህርት ቤት ሲስተም)፣
- ከቀረበው ወይም እምቢ ከተባለው አነሳሽ ወይም ለውጥ ጋር የተያያዘ የልጁ ችግር ማብራሪያ፣ ከችግሩ ጋር የተያያዙ ተጨባጭ ነገሮችን ጨምሮ፣ እና
- ለችግሩ የቀረበውን መፍትሔ- አቤቱታው በቀረበበት ጊዜ ለወገኑ እስከታወቀ ወይም እስከተገኘበት ድረስ።

ወላጁ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ ይህንን መረጃ የያዘ የፍትህ ሂደት አቤቱታ እስከሚያስገባ ድረስ ወላጁ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ (ወይም የወላጁ ጠበቃ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ ጠብቃ) የፍትህ ሂደት በችሎት ፊት ሊሰማለት አይችልም።

**ለፍትህ ሂደት አቤቱታው የሚሰጥ ምላሽ**

አንድ ሰው ወይም ድርጅት የፍትህ ሂደት አቤቱታ ሲያስገባ፣ ለልጁ ትምህርት ኃላፊ የሆነው የሕዝብ ድርጅት የሚከተሉትን ያደርጋል፦

- በነጻ ወይም በአነስተኛ ወጪ ማግኘት የሚቻሉትን የሕግ ወይም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች ለወላጅ ማስታወቅ፣
- የሥርዓት መከላከያ ደንቦች ሰነድ ቅጂ ለወላጅ መስጠት፣ እና
- ግልግል ማድረግ እንደሚቻል ለወላጅ ማስታወቅ።

የሕዝብ ድርጅቱ በፍትህ ሂደት አቤቱታ ውስጥ ወላጅ ስላነሳቸውን ጉዳዮች የሚናገር የቅድሚያ የጽሑፍ ማስትወቂያ ለወላጆች ካልላከ፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰው በ10 ቀን ውስጥ የሚከተሉትን የያዘ መልስ የሕዝብ ድርጅቱ ለወላጅ መላክ አለበት፦

- የሕዝብ ድርጅቱ ድርጊቱን/ቶችን የሚያቀርብበትን ወይም እምቢ የሚልበትን ምክንያት ማብራሪያ፣
- ሌላ ያጤናቸውን አማራጮችና እነዚህ አማራጮች ለምን እንደተተው የሚገልጽ ማብራሪያ፣
- የአካልስንኩል ወላጆች በሥርዓታዊ ደንቡ ሥር መከላከያ እንዳላቸው የሚናገር መግለጫ እና፣ ይህ ማስታወቂ የመጀመሪያ ግምገማ ማስተላለፊያ ካልሆነ፣ የሥርዓት መከላከያ ቅጂ የሚገኝበትን መንገድ፣ እና
- የ IDEAን አቅርቦቶች ለመረዳት የሚረዱ ምንጮች ምን እንደሆኑ ለወላጆች ማስታወቅ።

ይህ ምላሽ የሕዝብ ድርጅቱ የወላጁ የፍትህ ሂደት አቤቱታ በተገቢ ሁኔታ ያልተሟላ ከሆነ ይህንን ከማለት የሚከለክል አይደለም።

የፍትህ ሂደት አቤቱታው ሌላው ወገን (ወላጅ ወይም የሕዝብ ድርጅት) ለሌላው ወገን በፍትህ ሂደት አቤቱታ ውስጥ የተጠቀሱትን ጉዳዮች አንስቶ የሚያብራራ መልስ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰ በ 10 ቀን ውስጥ መስጠት አለበት።

## የማስታወቂያ ብቃት

የፍትህ ሂደት አቤቱታ የሚደርሰው ወገን፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታ መመዘኛዎችን አያሟላም በማለት መጥሪያ በደረሰው በ 15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለOAH እና ለሌላኛው ወገን በጽሑፍ ካላስታወቀ በስተቀር፣ የፍትህ ሂደት የተጠየቀበት ማስታወቂያ በቂ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። የተባለውን ማስታወቂያ ድክመት በተመለከተ የቀረበው የጽሑፍ ማስታወቂያ በደረሰው በ አምስት (5) ቀናት ውስጥ OAH ቀደም ሲል የቀረበው የፍትህ ጥያቄ ማስታወቂያ መመዘኛዎችን የሚያሟላ እንደሆነ ይወስናል፣ ከዚያም ለሁለቱም ወገኖች በጽሑፍ ያሳውቃል።

አንድ ወገን፣ ሌላኛው ወገን ስምምነቱን በጽሑፍ ካረጋገጠለትና ከታች በተመለከቱት መሠረት ችግሩን በእርቅ ስብሰባ ተገናኝቶ ለመፍታት ዕድል ከተሰጠው፣ ወይም የፍትህ ሂደቱ ሲሰማ ከ አምስት (5) ቀናት ያልበለጠ ጊዜ ሲቀረው OAH የፈቀደ ከሆነ ብቻ፣ ለፍትህ ሂደት ያቀረበውን ጥያቄ ማሻሻል ይችላል። ለእርቅ ስብሰባውና ለፍትህ ሂደቱ የሚሰጠው የጊዜ ሰሌዳ የተሻሻለው የፍትህ መጠየቂያ ማስታወቂያ እንደገና ሰቀርብ ጀምሮ ይሆናል።

## በፍትህ ሂደቶች ጊዜ የልጁ ሁኔታ/ቦታ

አንድ በአስተዳደራዊ በፍርድ ቤት የተያዘ ጉዳይ ገና በመካሄድ ላይ ባለበት ወቅት (ስነ ምግባር ክፍል ሥር የተጠቀሱትን ሳይጨምር)፣ ወላጆችና የሕዝብ ድርጅቱ በተቃራኒው እንዲሆን ካልተስማሙ በስተቀር፣ ተማሪው አሁን ባለበት የትምህርት ቦታው መቆየት ይኖርበታል። የፍትህ ሂደቱ ቀደም ብሎ ወደ ሕዝብ ትምህርት ቤት የማስገባት ቀዳሚ ማመልከቻን የሚያካትት ከሆነ፣ ተማሪው፣ በወላጆች ስምምነት፣ ሁሉም የፍትህ ሂደቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተማሪው በሕዝብ መርሀ ግብር ውስጥ መግባት ይኖርበታል። የALJው ውሳኔ፣ ወላጆች ለልጃቸው የቦታ ለውጥ መደረጉ ተገቢ ነው ከሚሉት ጋር የሚስማማ ከሆነ፣ ተከታታይ የይግባኝ ጥያቄዎችም በሚስተናገዱበት ወቅት ሁሉ፣ ያ የትምህርት ምድብ ቦታ የተማሪው የወቅቱ ምድብ ቦታ ሆኖ ይቆያል።

## ችግሩን የመፍታት ሂደት

በወላጆች የቀረበውን የፍትህ ሂደት ጥያቄ ማስታወቂያ ከደረሰው ከ15 ቀናት ውስጥ፣ እንደዚሁም የፍትህ ሂደት ጥያቄው ለመታየት ከመጀመሩ ቀደም ብሎ፣ የሕዝብ ድርጅቱ በወላጆችና በወረዳው እንደታመነበት ሁሉ በማስታወቂያው ላይ ስለተገለጹት እውነታዎች ዝርዝር እውቀት አላቸው ከሚባሉት አግባብነት ካላቸው የግል የትምህርት መርሀ-ግብር (IEP) ቡድን አባል/አባላት ጋር በጋራ ስብሰባ ያደርጋል። ስብሰባውም፦

- በሕዝብ ድርጅቱ ስም ውሳኔ የማድረግ ሥልጣን ያለው የሕዝብ ድርጅቱ ተወካይን ማካተት አለበት፣ <u>እና</u>
- ወላጁ ጠበቃ ካላመጣ በስተቀር የሕዝብ ድርጅቱን የሚወክል ጠበቃ ማካተት አይችልም።

ወላጁና የሕዝብ ድርጅቱ ስብሰባው ላይ የሚገኙትን አግባብነት ያላቸውን የ IEP ቡድን አባሎች ይወስናሉ።

የስብሰባው ዓላማ ወላጅ ስለ ፍትህ ሂደት አቤቱታውና አቤቱታው የተመሠረተበት ተጨባጭ ነገሮች የሕዝብ ድርጅቱ አለመግባባቱን የመፍታት ዕድል እንዲኖረው ለመነጋገር ነው።

የችግር መፍቻ ስብሰባው አላስፈላጊ የሚሆነው፦

- ወላጅና የሕዝብ ድርጅቱ ስብሰባውን ለመተው በጽሑፍ ሲስማሙ፣
- ወላጅና የሕዝብ ድርጅቱ ግልግልን ለመሞከር ሲስማሙ፣ ወይም
- የሕዝብ ድርጅቱ የፍትህ ሂደት አቤቱታውን ያነሳሳ ከሆነ።

የሕዝብ ድርጅቱ ወላጅ አጥጋቢ ሆኖ እስከሚያገኘው ድረስ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰው በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ችግሩን ካልፈታ (የችግሩ መፍትሔ ወቅት)፣ የፍትህ ሂደት ይግባኙ ሊከሰት ይችላል።

የመጨረሻ ውሳኔ መስጫው የ45 ቀን የጊዜ ገደብ የሚጀምረው የችግሩ መፍትሔ ወቅት ካለቀ ከ30 ቀን በኋላ ነው፣ ከዚህ በታች ከ "<u>የ30 ቀን የጊዜ ሰሌዳው ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች</u>" ወይም "<u>አፋጣኝ የጊዜ ሰሌዳዎች</u>" የሚሉት ክፍሎች ወስጥ ከተጠቀሱት አጋጣሚዎች አንዱ ካልተከሰተ በስተቀር።

## የ30 ቀን የጊዜ ሰሌዳው ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች

ችግሩን የመፍቻ የጊዜ ገደቡን ለማራዘም ወላጅና የሕዝብ ድርጅቱ ካልተስማሙ፣ የፍቺ ሥርዓቱን ይቅር ብለው ካልተውት፣ ወይም ግልግል ካልተጠቀሙ በስተቀር፣ የወላጅ የመስማሚያ ስብሰባ ውስጥ ከመገኘት መቅረት መፍትሔ የማግኛ የሥርዓቱንና የይግባኙን የጊዜ ገደቦች ስብሰባው እስከሚደረግ ድረስ ያዘገያል።

ተገቢ ጥረቶች አድርጎ፣ እነዚህንም ጥረቶች በሰነድ ከተያዙ በኋላ፣ የሕዝብ ድርጅቱ የመፍትሔ መፈለጊያ ስብሰባው ውስጥ ወላጆችን ተሳታፊ ለማድረግ ካልቻለ፣ የመፍትሔ ወቅቱ ካለቀ ከ30 ቀናት በኋላ የሕዝብ ድርጅቱ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በALJ እንዲሰረዝ መጠየቅ ይችላል። የሕዝብ ድርጅቱ ያደረጋቸው ጥረቶችን የያዘው ሰነድ፣ ለሁሉም ተስማሚ የሆነ የመገናኛ ሰዓትና ቦታ የሞከረበትን እንደሚከተሉት ዓይነት ሬኮርዶች ማሳየት አለበት፦

- በስልክ ለማግኘት የተደወለባቸው ወይም የተሞከረባቸው የዝርዝር ሬኮርዶችና የስልክ ጥሪዎቹ ውጤቶች፥
- ለወላጅ የተላከ ማንኛውም ዓይነት ደብዳቤ ቅጂና ማንኛውም የተገኘ ምላሽ፣ እና
- ወደ ወላጆች ቤት ወይም መሥሪያ ቤት የተደረጉ ጉብኝቶችና ውጤቶቻቸው በዝርዝር ሬኮርዶች።

የሕዝብ ድርጅቱ የመትሔ ስብሰባውን የወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማስታወቂያ በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ካላደረገ <u>**ወይም**</u> በመፍትሔ ስብሰባ ውስጥ ካልተሳተፈ፣ ወላጅ የይግባኝ ችሎቱ ተጀምሮ ውሳኔው በ45 ቀናት ውስጥ እንዲሰጠው ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።

ወላጁና የሕዝብ ድርጅቱ የመፍትሔ ስብሰባው እንዲቀር በጽሑፍ ከተስማሙ፣ የፍትህ ሂደት ችሎቱ የ45 ቀን የጊዜ ገደብ በማግስቱ ይጀምራል።

ግልግሉ ወይም የመፍትሔ ስብሰባው ከተጀመረ በኋላ ወላጁና የሕዝብ ድርጅቱ ስምምነት እንደሌለ በጽሑፍ ከተስማሙ፣ የፍትህ ሂደት ችሎቱ የ45 ቀን የጊዜ ገደብ በማግስቱ ይጀምራል።

ወላጁና የሕዝብ ድርጅቱ ግልግልን ለመሞከር ከተስማሙ፣ የ30 ቀን የችግር መፍቻው የጊዜ ገደብ ሲያበቃ፣ ሁለቱም ወገኖች ስምምነት እስከሚደርሱ ድረስ ግልግሉን ለመቀጠል በጽሑፍ መስማማት ይችላሉ። ሆኖም ወላጁ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ ከግልግሉ ተቶ ከወጣ፣ የፍትህ ሂደት ችሎቱ የ45 ቀን የጊዜ ገደብ በማግስቱ ይጀምራል።

## የችግሩን መፍትሔ ስምምነት

ላለመግባባቱ መፍትሔ ስብሰባው ላይ ከተገኘለት፣ ወላጁና የሕዝብ ድርጅቱ የሚከተለው ዓይነት በሕግ የሚያስገድድ ስምምነት ውስጥ መግባት አለባቸው፦

- በወላጅና የሕዝብ ድርጅቱ በስምምነቱ እንዲረጋ የሚያስችል ሥልጣን ያለው የሕዝብ ድርጅቱ ተወካይ የተፈረመ፣ <u>እና</u>
- በማንኛውም በአውራጃው መሥራት በሚችል የስቴት ፍርድ ቤት (ይህንን ዓይነት ክስ ሊሰማ የሚችላ የስቴት ፍርድ ቤት) ወይም የፌዴራል አውራጃ ፍርድ ቤት ውስጥ።

በስብሰባው ውጤት ምክንያት ወላጅና የሕዝብ ድርጅቱ ስምምነት ላይ ቢደርሱ፣ ማንኛውም ወገን ስምምነቱን በሶስት (3) የሥራ ቀናት ውስጥ ሊያፈርሱት ይችላሉ።

## የፍትህ ሂደት ችሎት

በአለመግባባት ውስጥ ያለው ወላጅ ወይም የሕዝብ ድርጅት፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታ በሚያቀርብበት ጊዜ፣ ወገን ያልያዘ የፍትህ ሂደት ችሎት የማግኘት ዕድል አለው።

የአስተዳደር ሕግ ዳኛ (ALJ)፦

- የአስተዳደራዊ ይግባኞች ቢሮ ተቀጣሪ ነው፣
- ከይግባኙ ዓላማ ጋር የሚጋጭ የግል ወይም የሙያ ጥቅም አያገኝበትም፣

- ስለ IDEA አቅርቦቶች፣ ከ IDEA ጋር የተያያዙ ፌዲራልና የስቴት ደንቦችና የ IDEA ሕጋዊ ትርጓሜዎች የሚያውቅና የሚረዳ ነው፣ እና
- ይግባኞችን የማስተዳደር፣ ውሳኔ የማድረግና የመጻፍ፣ ሁልጊዜ አንድ ዓይነትና ተገቢ የሆነ መደበኛ የሕግ አሠራር እውቀትና ችሎታ አለው።

**<u>የፍትህ ሂደት አቤቱታ ርእስ</u>**

የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማመልከቻውን የሚያስገባው የአቤቱታው ወገን (ወላጁ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ)፣ ሌላው ወገን ካልገተስማማ በስተቀር፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታው ላይ ያልተነሱ ጉዳዮችን ማንሳት አይችልም።

**<u>የይግባኝ መብቶች</u>**

ማንኛውም በፍትህ ሂድቱ ተካፋይ የሚሆን ወገን (የIDEAን ሥርዓታዊ መንገዶች የሚመለከት ይግባኝን ጨምሮ) የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፦

- በአማካሪዎችና የአካለስንኩላን ልጆች ችግር ልዩ እውቀትና ሥልጠና ባላቸው ግለሰቦች መታጀብና ከነሱም ምክርን የማግኘት መብቶች፣
- ማስረጃን የማቅረብና የመከራከር፣ ምስክሮችም እንዲገኙና መስቀለኛ ጥያቄን የማድረግ መብቶች፣
- የፍትህ ሂደቱ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ 5 የሥራ ቀናት በፊት ለተካፋይ ወገኖች ያልተገለጸ ማኛውንም ዓይነት ማስረጃን የመከልከል መብት፣
- የፍትህ ሂደቱን ሬኮርድ ቃል በቃል በጽሑፍ፣ ወይም በወላጆች ምርጫ፣ በኤሌክትሮኒክ ቅጂ የማግኘት መብት፣ እና
- በወላጆች ምርጫ፣ በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮትኒክስ የእውነት ማጣራት ሂደቶችንና ውሳኔዎችን የማግኘት መብቶች።

**<u>በግልጽ ስለማውጣት ተጨማሪ መረጃ</u>**

የፍትህ ሂደት ይግባኝ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ አምስት (5) የሥራ ቀናት በፊት፣ እያንዳንዱ የሂደቱ ተካፋይ ወገን፣ ለሌሎቹ ሁሉም ተካፋይ ወገኖች ሁሉ፣ በዚያን ቀን የተጠናቀቁ ግምገማዎችንና በተካፋይ ወገኑ ግምገማ ላይ የተመሠረቱ ሆነው በፍትህ ሂደቱ ላይ ተካፋይ ወገኑ ሊጠቀምባቸው ያሰባቸውን አስተያየቶች ሁሉ ይገልጻል።

አንደኛው ወገን ከሌላኛው ወገን ፈቃድ ሳያገኝ ግምገማዎችን ወይም አስተያየቶችን በፍትህ ሂደቱ ላይ ለማስማት ቢፈልግ፣ ከላይ የተጠቀሰውን ሁኔታ ካላሟላ ALJው ሊያግደው ይችላል።

**<u>የወላጅ መብቶች</u>**

ወላጁ የሚከተሉት መብቶች አሉት፦

- ልጁ እንዲገኝ ማድረግ፣
- ይግባኙን ለሕዝብ መክፈት፣ እና
- የይግባኙ ሬኮርድ፣ የተጨባጭ ነገሮች ግኝቶችና ውሳኔዎች በነጻ ለእርስዎ ሊሰጡዎት ይገባል።

**<u>የይግባኝ ውሳኔ</u>**

አንድ ተማሪ የነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) አግኝቶ እንደሆነ ለማረጋገጥ፣ አንድ ALJ በተጨባጭ በተረጋገጠ ማስረጃ ላይ በመመሥረት ይወስናል። የሥርዓታዊ ጥሰትን በሚመለከት ለሚቀርብ ያልተጣራ ክስ፣ አንድ ALJ ፣ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን በማጤን አንድ ተማሪ FAPE እንዳላገኘ ሊደረስበት ይችላል፦

- ልጁ FAPE ከማግኘት መብቱ አደናቅፎት ከሆነ፣
- ልጁ FAPE እንዲያገኝ በሚደረገው የውሳኔ ሥርዓታዊ አሠራር ላይ ወላጆች የመካፈል ያላቸውን ዕድል በከፍተኛው አደናቅፎት ከሆነ፣ ወይም
- የትምህርት ጥቅም ከማግኘት ያስቀረ ከሆነ።

ከዚህ በላይ የተገለጹት ማንኛውም አቅራቦቶች ALJው የሕዝብ ድርጅቱ በ ፌዴራል ደንቦች IDEA (34 CFR 300.500 እስከ300.536) በክፍል B ሥር ያሉት ሥርዓታዊ መከላከያዎች አስፈላጊ ነጥቦችን እንዲያከብር ከማዘዝ አይከለክሉትም።

**ለብቻው የተለየ የፍትህ ሂደት አቤቱታ**

የ IDEA የሥርዓታዊ መከላከያዎች ክፍል ውስጥ ወላጅን ከዚህ በፊት ካመለከተው የፍትህ ሂደት አቤቱታ ጉዳይ ጋር ምንም የማይያያዝ ለብቻው የተለየ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ከማስገባት የሚከለክለው ምንም ነገር የለም።

**የጊዜ ሰሌዳዎችና የችሎት አመቺነት**

የ30 ቀን ጊዜ የሚሰጣቸው የመፍትሔ ስብሰባዎች ወቅት ካለቀ በኋላ ከ45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ ከዚህ በታች ከ "የ30 ቀን የጊዜ ሰሌዳው ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች" ወይም "አፋጣኝ የጊዜ ሰሌዳዎች" ውስጥ እንደተገለጸው፦

- በይግባኙ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ተደርጓል፣ እና
- የውሳኔው ቅጂ ለእያንዳንዱ የክስ ወገን ተልኳል።

ማንኛውም ወገን ጥያቄ ካቀረበ ALJው ከ45 ቀኖቹ የበለጠ የተወሰነ የጊዜ ማራዘም ሊሰጥ ይችላል።
እያንዳንዱ ይግባኝ መደረግ ያለበት ለወላጁ ወይም ለልጁ አግባብ ባለው አመቺ ሰዓትና ቦታ መሆን አለበት።

**የተፋጠኑ የጊዜ ሰሌዳዎች**

የሚቀጥሉትን በተመለከተ በአንድ አካለስንኩል ልጅ ስም የፍትህ ሂደት አቤቱታ በተደረገ ጊዜ፣ የሕዝብ ድርጅቱ የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፦

- አካለስንኩል የሆነ ልጅ በአሁኑ ጊዜ ትምህርት ቤት ያልተመዘገበ ወይም ትምህርት ቤት የማይሄድ፣
- አካለስንኩል የሆነን ልጅ በመሸጋገሪያ አማራጭ የትምህርት ቦታ በተመደበ ጊዜ፣ ወይም
- የገለጻ ውሳኔ።

የፍትህ ሂደት አቤቱታው በገባ በ20 የትምህርት ቀናት ውስጥ የፍትህ ችሎቱ መካሄድ አለበት። ALJው ይግባኙ ካለቀ በኋላ በ10 ቀን ውስጥ ውሳኔ ምድረግ አለበት። የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማስታወቂያ በደረሰ በሰባት (7) ቀናት ጊዜ ውስጥ የመፍትሔ መፈለጊያ ስብሰባ መደረግ አለበት፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ለሁለቱም ወገኖች አጥጋቢ እስከሆነ ድረስ ካልተፈታ በስተቀር የፍትህ ሂደት ይግባኙም ይቀጥላል።

**የፍርድ መጨረሻነት**

ወላጆች ወይም የሕዝብ ድርጅቱ ይግባኝ ካላሉ በስተቀር የ ALJው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። በግኝቶቹና በውሳኔዎቹ ይልተደሰተ ማንኛውም ወገን ይግባኙ ላይ የታየውን አቤቱታ በተመለከተ የማህበራዊ እርምጃ ሊያመጣ ይችላል።

## **ይግባኝ**

ማንኛውም የይግባኝ ወገን በንትርክ ላይ ያለው ጉዳይ መጠን ምንም ያክል ይሁን፣ በሜሪላንድ ሕግ መሠረት የመጨረሻው ውሳኔ በተሰጠ በ120 ቀናት ውስጥ፣ በማንኛውም ተወዳዳሪ ሥልጣን ባለው የመንግሥት ፍርድ ቤት ወይም በማንኛውም የዩናይትድ ስቴትስ የወረዳ ፍርድ ቤት ለማህበራዊ እርምጃ ማመልከት ይችላሉ።

ለማንኛውም እርምጃ፣ ፍርድ ቤቱ፦

- የአስተዳደራዊ ሂደቶቹን ሬኮርዶች ማግኘት፣
- በወላጆች ወይም በህዝባዊ ድርጅቱ ጥያቄ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ያዳምጣል፣ እና
- ውሳኔውንም ሚዛን የሚደፋ ሆኖ በተገኘው ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ይወስናል፣ እና
- ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ብያኔ ይሰጣል።

በ IDEA ክፍል B ውስጥ መብቶችን፣ ሥርዓታዊ ሂደቶችን፣ ከአካለ ጎደሎነት ጋር የሚኖሩ አሜሪካውያን ድንጋጌ 1990 (Americans with Disabilities Act of 1990, Title V of the Rehabilitation Act of 1973 (Section 504))፣ የ1973 ዓ.ም.

የመልሶ ማቋቋሚያ/ማገገሚያ ድንጋጌ ርዕስ V (ክፍል 504)፣ ወይም ከአካለ ጎደሎነት ጋር የሚኖሩ ተማሪዎች መብቶችን የሚጠብቁ ሌሎች የፌዴራላዊ ሕጎች መሠረት፣ በሕገ መንግሥቱ የተፈቀዱ የመፍትሄ መድሀኖችን የሚከለክል ወይም የሚገድብ አንዳችም ነገር የለም። በነዚህ ሕጎች ሥር ለማህበራዊ እርምጃ ከማመልከት በፊት፣ ወላጆች ወይም ሕዝባዊ ድርጅቱ ከOAH ጋር የሚደረገውን ማናቸውንም የፍትህ ሂደቶችን በሙሉ አሟጠው የጨረሱ መሆን የሚገባቸው ከሚሆን በስተቀር። ይህ ማለት በሌሎች ሕጎች ሥር ወላጆች በ IDEA ሥር የሚያገኙትን መፍትሔዎች ሊያገኑ ይችላሉ፣ ግን በነዛ ሕጎች ሥር መፍትሔ ለማግኘት ከፈለጉ፣ ቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዳቸው በፊት ወላጆች መጀመሪያ በ IDEA ሥር የሚገኙትን አስተዳደራዊ መፍትሔዎች መጠቀም አለባቸው (ለምሳሌ የፍትህ ሂደት አቤቱታውን፣ የመፍትሔ መፈለጊያ ስብሰባውን፣ እና ወገን ያልያዘ የፍትህ ሂደት ሥርዓቶች)።

## የጠበቆች ክፍያዎች

በማንኛውም በ IDEA ሥር የመጣ እርምጃ ወይም ሂደት ውስጥ፣ ፍርድ ቤቱ ተገቢ የሆኑ የጠበቃ ክፍያዎች ለሚከተሉት ሊሰጥ ይችላል፦

- የአንዱ ወገን የሆነው የአካለስንኩሉ ተማሪ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች፣
- ቅሬታን ወይም በጣም አልባሌ፣ ምክንያት አልባ፣ ወይም መሠረተቢስ በሆኑ ማስረጃዎች ምክንያትነት ለተወሰዱ የክታታይ እርምጃዎች ቅሬታቸውን ካስመዘገቡ ወላጆች በተቃራኒ ለሚቆመው ለወቅቱ ተጻራሪ ወገን፣ ማለት MSDE ወይም ማንኛውም ሌ ሕዝባዊ ድርጅት፣ ወይም የቀረበው ክስ አልባሌነት፣ ምክንያት አልባነት፣ ወይም መሠረተ ቢስነት ግልጽ ከሆነ በኋላም ክሱን ለሚቀጥል የወላጆች ጠበቃ፣ ወይም
- ከወላጆች ጠበቃ በተቃራኒ ለሚቆም ማንኛውም የወቅቱ ወገን ማለትም MSDE ወይም ሌላ የሕዝብ ድርጅት፣ ወይም ከወላጅ በተጻራሪ፣ የወላጆች ቅሬታ ወይም የተከታታይ እርምጃዎች ምክንያት እንዲያው አግባብነት ለጎደለው ማንኛውም ዓላማ፣ ለምሳሌም ለማበሳጨት፣ አላስፈላጊ የጊዜ መገተትን ለመፍጠር፣ ወይም አላግባብ የፍርድ ቤት ክስ ወጪን ለመጨመር በሚል አዝማሚያ ቀርቦ ከሆነ።

ለቀረቡ አገልግሎቶች ዓይነትና ጥራት የሚፈቀዱ ክፍያዎች፣ ድርጊቱ/እርምጃው በተነሳበት ማህበረሰብ የወቅቱ ስሌት ላይ የተመሠረቱ መሆን ይገባቸዋል። ክፍያዎቹን በማስላት ጊዜ፣ ተጨማሪ ጉርሻ (ቦነስ) ማከል ወይም ብዜትን መጠቀም አይቻልም።

በሚከተሉት ሁኔታዎች ሥር ክፍያዎች ላይፈቀዱ ይችላሉ፦

- ለማንኛውም የIEP ቡድን ስብሰባ፣ ስብሰባው የተጠራው በፍትህ ሂደቱ ውጤት ወይም በዳኝነት እርምጃው ምክንያት ካልሆነ በስተቀር፣
- ለፍትህ ሂደት ማመልከቻ ከመግባቱ ቀደም ብሎ ለተደረገ ግልግል፣
- ለእርቅ/መግባቢያ ስብሰባዎች፣ እና
- በሚከተሉት ሁኔታዎች ሰበብ፣ ለወላጅ የጽሑፍ መግለጫ መሰጠቱን ተከትሎ ለቀረቡ አገልግሎቶች፦
  - የጽሑፍ መግለጫው እንዲሰጥ የተደረገው፣ በፌዴራላዊው የማሕበራዊ ሥነሥርዓት ደንቦች፣ የሥነሥርዓት ደንብ 68፣ ሥር በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ከሆነ፣ ወይም በአስተዳደራዊ የጉዳይ ማጣራት ሂደት መሠረት፣ ጉዳዩ መታየት ከሚጀመርበት ከአሥር ቀናት በሆነ ጊዜ ቀደም ብሎ ከሆነ፣
  - የቀረበው አቅርቦት በአሥር ቀናት ውስጥ ተቀባይነት ካላገኘ፣ እና
  - ፍርድ ቤቱ፣ ጉዳዩ በተስተናገደበት ሂደት ላይ ወላጆች ያገኙት መፍትሄ ለወላጆች ከማሳረጊያ ስምምነት ላይ ከመድረስ የተሻለ ያልነበረ ሆኖ ካገኘው። ወላጁ የቀረበውን የማሳረጊያ ስምምነት ላለመቀበል እምቢ ማለቱ አሳማኝነት ካለው፣ ክፍያዎችና ወጪዎች ይፈቀዱለታል።

በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት ክፍያዎች ሊቀነሱ ይችላሉ፦

- ወላጁ ወይም የወላጁ ጠበቃ ጭቅጭቁን ለመፍታት ከሚወሰደው ጊዜ በላይ ያለአግባብ ካጓተቱት፣
- የክፍያው መጠን፣ በወቅቱ ላይ ባለው፣ በአግባቡ የመጣጣኝ ችሎታ፣ እውቀና እና የሙያ ልምድ ላላቸው ጠበቆች በማህበረሰቡ ውስጥ ለተመሳሳይ አገልግሎቶች ከሚፈቀደው የሰዓት ክፍያ ስሌት በላይ አላግባብ በልጦ ከተገኘ።

- ጉዳዩ የታየበት ባሕርይና ሁኔታ ሲጤን፣ የወሰደው ጊዜና የአገልግሎት መጠን በጣም የተንዛዛ ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም
- የፍትህ ሂደት ጥያቄውን ሲያቀርብ፣ ጠበቃው ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን ያላቀረበ ከሆነ።

በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት፣ ክፍያዎች አይቀነሱም፦

- የሕዝብ ድርጅቱ የመፍትሄ ሂደቱን ካራዘመው፣ ወይም
- በሥርዓታዊ መከላከያዎች መስፈርቶች ላይ ጥሰት ተፈጽሞ ነበር።

ወላጆች ለጠበቆቻቸው ያወጧቸውን ወጪዎቻቸውን መልሰው ለመቀበል የሚችሉት በ IDEA ውስጥ የተደነገጉትን ሁኔታዎች በማሟላታቸው ላይ የሚመሠረት በመሆኑ፣ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ከጠበቆቻቸው ጋር መወያየት ይኖርባቸዋል።

## የተያያዘ

# የIDEA የአለመግባባት ፍቺ አሠራሮች ማወዳደሪያ ሠንጠረዥ

| | ግልግል | የፍትህ ሂደት አቤቱታ | አለመግባባት የመፍቻ መንገድ | የስቴት አቤቱታ |
|---|---|---|---|---|
| የሥርዓቱ አነሳሽ ማን ሊሆን ይችላል? | ወላጅ ወይም የሕዝብ ድርጅት፣ ለሁለቱም በፈቃደኝነት መሆን አለበት | ወላጅ ወይም የሕዝብ ድርጅት | ተከራካሪ ወገኖች ለማስቀረት ወይም ግልግልን ለመጠቀም ካልወሰኑ በስተቀር፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰው ጊዜ የሕዝብ ድርጅቱ የመፍትሔ መፈለጊያ ስብሰባውን ያዘጋጃል | ማኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት፣ ከስቴቱ ውጪ ያሉትንም ጨምሮ |
| ማመልከቻ የማስገቢያ የጊዜ ግደቡ ምን ያክል ነው? | ምንም የተጠቀሰ የለም | ከመጠነኛ ጥበቃዎች ወገኑ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከነበረበት ጊዜ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ[1] | አንድ ወላጅ ባስገባው የፍትህ ጊደት አቤቱታ ምክንያት የሚወሰን | የሕግ ጥሰቱ ከተከሰተበት ቀን በኋላ እስከ 1 ዓመት ጊዜ ውስጥ |
| መፈታት የሚችሉት ጉዳዮች ምንድን ናቸው? | በክፍል 300 ሥር ያለ ማንኛውም ጉዳይ፣ የፍትህ ሂደት አቤቱታውን ከማስገባት በፊት የተነሱ ጉዳዮችን ጨምሮ (ይህ የማይሆንባቸው ልዩ ጉዳዮች አሉ)[2] | መታወቂያን፣ ግምገማን ወይም የትምህርት ምደባን ወይም የነጻ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት አቅርቦትን የተመለከተ ማንኛውም ጉዳይ (ይህ የማይሆንባቸው ልዩ ጉዳዮች አሉ) | የወላጁ የፍትህ ሂደት አቤቱታ ውስጥ ከተነሱት ጉዳዮች ጋር አንድ ዓይነት | የ IDEA ክፍል B ወይም ክፍል 300 ተጥሰዋል የተባሉ ሕጎች |
| ጉዳዮቹን ለመፍታት የተሰጠው የጊዜ ገደብ ምን ያክል ነው? | ምንም የተጠቀሰ የለም | ለጊዜ ገደቡ የተወሰነ የጊዜ ማራዘም ካልተሰጠ በስተቀር፣ የጉድዩ መፍቻ የጊዜ ገደብ ካለቀ ከ45 ቀናት በኋላ[3, 4] | ተከራካሪ ወገኖቹ ስብሰባውን ለመተው ወይም ግልግልን ለመጠቀም በጽሑፍ ካልተስማሙ በስተቀር፣ የወላጆቹ የፍትህ ሂደት አቤቱታ በደረሰ በ15 ቀን ውስጥ የሕዝብ ድርጅቱ የችግሩን መፍቻ ስብሰባ መጥራት አለበት<br><br>ተከራካሪ ወገኖቹ በተቃራኒው ካልተስማሙ ወይም ወላጁ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ በችግር መፍቻ ስብሰባው ሳይሳተፍ ከቀረ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ የወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታው በደረሰው በ15 ቀን ውስጥ የችግር መፍቻ ስብሰባ ካልጠራ በስተቀር የችግር መፍቻ የጊዜ ገደብ የወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ጊዜ ድረስ ውስጥ[3, 5, 6, 7] | የጊዜ ማራዘም ካልተፈቀደ በስተቀር፣ አቤቱታው ከደረሰ ከ60 ቀናት በኋላ [8] |
| ጉዳዮቹን የሚፈታው ማነው? | ወላጅ ወይም የሕዝብ ድርጅት ከ ገላጋይ ጋር<br><br>ሂደቱ በፈቃደኝነት የሚሆን ሲሆን ሁለቱም ወገኖች ለማንኛውም መፍትሔ መስማማት አለባቸው | የይግባኝ ባለሥልጣን/የአስተዳድር ህግ ዳኛ(ALJ) | ወላጅና የሕዝብ ድርጅት<br><br>ሁለቱም ወገኖች ለማንኛውም መፍትሔ መስማማት አለባቸው | የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል[9] |

[1] በሚከተሉት ምክንያቶች ወላጅ የፍትህ ሂደት ከማስገባት ከተከለከለ የጊዜ ገደቡ አይያዝም፦ (1) የፍትህ ሂደት አቤቱታ የገባበትን ምክንያት ችግሩ ተፈቷል ብሎ የሕዝብ ድርጅቱ በግልጽ በሐሰት ከገለጸ፣ ወይም (2) የሕዝብ ድርጅቱ በ IDEA ሥር ክፍል 300 መሠረት ለወላጅ መሠጠት የነበረበትን መረጃ ካስቀረ (34 C.F.R. §300.511(f))።

[2] ይህ የማሆንባቸው ልዩ ጉዳዮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦ የመጀመሪያ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ስምምነትን ወላጅ አልሰጥም ያለበትን ለመሻር የሕዝብ ድርጅት የፍትህ ሂደት አቤቱታ ወይም ግልግል መጠቀም አይችልም (34 C.F.R. §300.300(b)(3))፣ በወላጅ በኩል የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የተመደበን ወይም በቤት ውስጥ ትምህርት የሚማር ልጅን የመጀመሪያ ግምገማን ወይም ዳግም ግምገማን ስምምነትን ወላጅ አልሰጥም ያለበትን ለመሻር የሕዝብ ድርጅት የፍትህ ሂደት አቤቱታን ወይም ግልግልን መጠቀም አይችልም፣ (34 C.F.R. §300.300(c)(4)(i))፣ በወላጆች ምክንያት የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የተመደቡ ልጆች ወላጆች የፍትህ ሂደት አቤቱታ የማስገባት መብት ያላቸው የሕዝብ ድርጅቱ የልጁን አስፈላጊ ነጥቦች በሚከተለው ሳያሟላ ሲቀር ብቻ ነው (34 C.F.R. §300.140)፣ የሕዝብ ድርጅቱ ከፍተኛ ጥራት ያለው አስተማሪ ሳያቀርብ ቢቀር የፍትህ ሂደት አቤቱታ ማስገባት አይቻልም፣ ግን የስቴት ትምህርት ድርጅት (SEA) ጋር የስቴት አቤቱታ ማስገባት ይቻላል (SEA) (34 C.F.R. §300.156(e))።

[3] በስነ ምግባር ሂደቶች ምክንያቶች የፍትህ ሂደት አቤቱታ ለአፋጣኝ ይግባኝ ቢደረግ፣ ወይም ልጁ በወቅቱ ትምህርት ቤት ተመዝግቦ ካልሆህነ ወይም ትምህርት ቤት እየሄደ ካልሆነ፣ ችግሩን የመፍቻ የጊዜ ገደቡ 15 ቀናት ነው (ስብሰባው በ7 ቀናት ውስጥ ተደርጎ)። ሁለቱም ወገኖች አጥጋቢ ሆኖ እስካገኙት ድረስ ችግሩ ካልተፈታ፣ ይግባኙ ጥያቄው በቀረበ በ20 ቀን ውስጥ መካሄድ አለበት፣ ውሳኔውም ይግባኙ ባለቀ በ10 የትምህርት ቀናት ጊዜ ውስጥ መሰጠት አለበት (34 C.F.R. §300.532(c) and COMAR 13A.05.01.15)።

[4] የግባኝ ባለሥልጣን/ALJ ማንኛውም ወገን በጠየቀ ጊዜ የተወሰነ የጊዜ ማራዘም ሊሰጥ ይችላል (34 C.F.R. §300.516(c))።

[5] ደንቦቹ ለመፍትሔ ለተሰጠው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ማስተካከል እንዲደረግ ይፈቅዳሉ። የፍትህ ሂደት የ45 ቀን የጊዜ ገደብ የሚጀምረው የሚከተሉት ሁኔታዎች ከሆኑ ከአንድ ቀን በኋላ ነው፦ (1) ሁለቱም ወገኖች የመፍትሔ ስብሰባውን ለመተው በጽሑፍ ይስማማሉ፣ (2) የግልግል ወይም የችግር መፍቻ ስብሰባው ከጀመረ በኋላ ግን የ30 ቀን የጊዜ ገደቡ ከማለቁ በፊት፣ ሁለቱም ወገኖች ስምምነት ላይ ሊደረስ እንደማይቻል በጽሑፍ ከተስማሙ፣ (3) የ30 ቀን የጊዜ መፍቻ ገደቡ ካለቀ በኋላ ግልግሉን ለመቀጠል ሁለቱ ወገኖች በጽሑፍ ተስማምተው፣ በኋላ ግን ወላጁ ወይም የሕዝብ ድርጅቱ ከግልግል ሂደቱ ለቅቆ ሲወጣ (34 C.F.R. §300.510 (c))።

[6] ወላጅ በመፍትሔ ማግኛ ስብሰባ ውስጥ አልሳተፍም ሲል ስብሰባው እስከሚደረግ ድረስ የመፍትሔውን ሂደትና የፍትህ ሂደት ችሎቱን የጊዜ ገደቦች ያጓትታል (34 C.F.R. §300.510(b)(3))።

[7] የሕዝብ ድርጅቱ የመፍትሔ ማግኛ ስብሰባውን የወላጅ የፍትህ ሂደት አቤቱታ በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ሳያደርግ ከቀረ ወይም የመፍትሔ ስብሰባ ውስጥ ሳይሳተፍ ከቀረ፣ የፍትህ ሂደት ይግባኙን የጊዜ ገደብ ለመጀምር ወላጅ የALJን ጣልቃ ገብነት ሊያስከትል ይችላል (34 C.F.R. §300.510(b)(5))።

[8] አንድ የተወሰነ አቤቱታን በተመለከተ ልዩ ሁኔታዎች ከተከሰቱ የስቴት አቤቱታውን የመፍቻ የጊዜ ገደቡ ሊራዘም ይችላል፣ ወይም ወላጁ (ወይም ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ፣ ግልግል ወይም ሌላ የችግር መፍቻ መንገድ በስቴት ሥርዓተ ሂደት ሥር ለግለሰብ ወይም ለድርጅት የሚገኝ ከሆነ) እና የሕዝብ ድርጅቱ ግልግል ለመጠቀም ወይም ስቴቱ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ ሌላ የችግር መፍቻ ዘዴ ለመጠቀም ከተስምሙ (34 C.F.R. §300.152(b)(1))።

[9] የMSDE የአቤቱታ አሠራር መንገዶች የሕዝብ ድርጅቱ ለአቤቱታ መልስ የሚሰጥበትን ዕድል፣ በሕዝብ ድርጅቱ ምርጫ፣ አቤቱታውን ለመፍቻ የመትሔ አቅርቦት፣ እና አቤቱታ ያቀረበው ወላጅና የሕዝብ ድርጅቱ በፈቃደኝነት ግልግል ለማድረግ እንዲስማሙ ዕድል ይሰጣል (34 C.F.R. §300.152(a)(3))። በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ፣ አቤቱታ አቅራቢውና የሕዝብ ድርጅቱ ችግሩን ለመፍታት MSDEን ሳይጠቀሙ አለመግባባቱን ሊፈቱ ይችላሉ።